# መመሪያ

በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከላት ለሚኖሩ የተዘጋጀ

AMHARISK



UDI
Utlendingsdirektoratet

# የርዕስ ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| | ውድ ኗሪ | 3 |
| ምዕራፍ 1 | ጥገኝነት ስለመጠየቅ | 5 |
| ምዕራፍ 2 | ጤና | 11 |
| ምዕራፍ 3 | ትምህርት | 17 |
| ምዕራፍ 4 | የኖርዌይ ማኅበረሰብ | 21 |
| | – የጥገኝነት ጥያቄ ሂደት ደረጃ በደረጃ | 26 |
| ምዕራፍ 5 | ሕጉን ማወቅ | 31 |
| ምዕራፍ 6 | ወደ አገር መመለስ | 37 |
| ምዕራፍ 7 | በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ሲሰጥዎ | 41 |
| ምዕራፍ 8 | ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂዎች | 49 |

# ውድ ኗሪ፣



**ስሜ መሃመድ ይባላል:: የኖርዌይ የኢሚግሬሽን ዳይሬክቶሬት (UDI) ይህንን ቡክሌት እንዳስተዋውቅ ጠይቆኛል:: እርስዎም ይህንን ቡክሌት ጠቃሚና ተግባራዊ ሆኖ እንደሚያገኙት ተስፋ አደርጋለሁ::**

እኔ ዶክተር ስሆን ወደ ኖርዌይ የመጣሁት በ2004 መጀመሪያ ላይ በስደተኛነት ነው:: በኖርዌይ ለረዥም ጊዜ ባልቆይም ስለ አገሪቷ ማወቅ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ እገነዘባለሁ:: ለአገሪቷ አዲስ እንደመሆንዎ መጠን ብዙ የሚማሩት ነገር እንዳለ ይገነዘባሉ:: ሆኖም የቻሉትን ያህል አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ መጣርዎ የኖርዌይ ሕይወትዎን ቀላል ያደርግልዎታል:: ልጆችዎ በተቻለ መጠን ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርት መቅሰም እንዲችሉ ስለ ኖርዌይ የትምህርት ሥርዓት ማወቅ ያስፈልግዎታል:: ሕግ እንዳይጥሱ ስለ ኖርዌይ ሕግ ማወቅ ግድ ነው:: የኖርዌይን ሕዝብ አኗኗርና የሥራ ሁኔታም መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው::

ሴቶች በተለይ ለእነርሱ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች ማወቅ ይኖርባቸዋል:: ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ከእነርሱ ሁኔታ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች ማወቅ የሚኖርባቸው ሲሆን ልጆችም እንደ ሁኔታቸው የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ማግኘት አለባቸው::

በኖርዌይ እንዲቆዩ ፈቃድ ከተሰጣቸው ይልቅ ማመልከቻቸው ውድቅ የተደረገባቸው ሰዎች የተለያየ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል::

በዚህ ቡክሌት ውስጥ የቀረበው መረጃ ሌሎች ብዙ ጉዳዮችን ጨምሮ በመቀበያ ማዕከሉ የመረጃ ፕሮግራም ውስጥ በዝርዝር ውይይት ይካሄድበታል:: የመረጃ ፕሮግራሙ ኖርዌይ ውስጥ መኖርን በተመለከተ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ብዙ ነገሮችን ያስገነዝብዎታል::

ይህ ቡክሌት በኖርዌይ እንዲኖሩ ተፈቀደልዎም አልተፈቀደልዎ ስለ መብቶችዎ፣ ኃላፊነትዎ እና በኖርዌይ ስለሚኖሩዎት አጋጣሚዎች እንዲያውቁ ለመርዳት ታስቦ የተዘጋጀ ነው::

በመቀበያ ማዕከሉ ቆይታዎ ወቅት መኖሪያውን፣ የእሳት አደጋን፣ ገንዘብን እንዲሁም ከማዕከሉ መጥፋትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ መመሪያ ያገኛሉ:: ከዚህም በተጨማሪ የመቀበያ ማዕከሉ ሠራተኞች የሐኪም እርዳታ ካስፈለግዎ ምን እንደሚያደርጉ ይነግሩዎታል:: የአካባቢውን የመጓጓዣ ዘዴ፣ ገበያ፣ ትምህርት ቤት እና መዋዕለ ሕጻናት አገልግሎቶች በተመለከተ እውቀት እንዲኖርዎ ያደርጋሉ::

ከዚህም በተጨማሪ በመቀበያ ማዕከላቱ ነዋሪዎች የሚሳተፉባቸው በርካታ ተግባራት አሉ:: በየትኛው እንቅስቃሴ መሳተፍ እንደሚችሉ መጠየቅ ይችላሉ::

**ለአገሪቷ አዲስ እንደመሆንዎ መጠን ብዙ የሚማሩት ነገር እንዳለ ይገነዘባሉ:: ሆኖም የቻሉትን ያህል አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ መጣርዎ የኖርዌይ ሕይወትዎን ቀላል ያደርግልዎታል::**

ይህ ቡክሌት በሚከተለው አድራሻ ይገኛል ፡-
www.nyinorge.no



“የጥገኝነት ጥያቄ ሲያቀርቡ አንድም ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቶ ሊቆዩ አሊያም ወደ አገርዎ ሊመለሱ ይችላሉ“

ምዕራፍ 1

# ጥገኝነት ስለመጠየቅ



በኖርዌይ እንዲኖሩ ፈቃድ ማግኘት አለማግኘትዎ የሚወሰነው የኖርዌይን ሕግና የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ ነው:: ይህ ምዕራፍ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ሲያቀርቡ ስለሚኖረው ሁኔታ ያብራራል::

በኖርዌይ ከለላ ማግኘት የሚያስፈልገው ማንኛውም ሰው ይህንን ከለላ ያገኛል:: ዩዲአይ የሚቀርቡለትን የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎች በሙሉ በጥንቃቄ የሚመረምረው ለዚሁ ነው:: የጥገኝነት ጥያቄ ሂደት የሚባለው ይህ ነው:: ማመልከቻዎቹ በጥንቃቄ የሚመረመሩበት ዓላማ በእርግጥ በኖርዌይ ከለላ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች በኖርዌይ እንዲኖሩ ለማድረግና ከለላ የማያስፈልጋቸው ደግሞ ኖርዌይን ለቀው እንዲወጡ ማድረግ ነው::

## የጥገኝነት ጥያቄ ሂደት

ዩዲአይ ሁሉም ሰው በእኩል መልክ መስተናገዱን ለማረጋገጥ ሲል እያንዳንዱን ማመልከቻ የሚመረምረው በተናጠል ነው:: እገሌ ከእገሌ ሳይባል የሁሉም ሰው ማመልከቻ በተመሳሳይ መንገድ በተመሳሳይ ህጎች መሠረት ይታያል::

በኖርዌይ የጥገኝነት ጥያቄ ሲያቀርቡ የኖርዌይ መንግሥት ከለላ እንዲሰጥዎ መጠየቅዎ ነው:: የኖርዌይ መንግሥት ማመልከቻዎን ሊቀበለውም ላይቀበለውም ይችላል:: ብዙ ጥገኝነት ጠያቂዎች ማመልከቻቸው ውድቅ በመደረጉ ወደ አገራቸው ለመመለስ ተገድደዋል::

ዩዲአይ ለእያንዳንዱ አመልካች ቃለ መጠይቅ በማድረግና ከቃለ መጠይቁ ያገኘውን መረጃ ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማጣመር አመልካቹ ለጥገኝነት ብቁ እንደሆነና እንዳልሆነ ይወስናል:: ዩዲአይ በትውልድ አገርዎ ስላሉት ሁኔታዎችም በጣም ብዙ የሚያውቃቸው ነገሮች አሉ::

## ጥገኝነት

ሕይወትዎን ወይም ነጻነትዎን አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ካለ ወይም ደግሞ በፖለቲካ አቋምዎ ምክንያት በደል ወይም ሰብዓዊነት የጎደለው ድርጊት ሊፈጸምብዎ የሚችልበት አጋጣሚ ካለ በኖርዌይ ጥገኝነት የመጠየቅ መብትዎ የተጠበቀ ነው:: በሃይማኖታዊ አቋምዎ ወይም የአንድ ብሔር ፣ ወገን ወይም ጎሳ አባል በመሆንዎ ምክንያት ከተሰደዱም ሁኔታው ተመሳሳይ ይሆናል::

ሴቶች በሴትነታቸው ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ዒላማ ከተደረጉ ጥገኝነት ሊሰጣቸው ይችላል:: በሚከተሉት የወሲብ ሕይወት

ሕይወትዎን ወይም ነጻነትዎን አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ካለ ወይም ደግሞ በደልና ሰብዓዊነት የጎደለው ድርጊት ሊፈጸምብዎ የሚችልበት አጋጣሚ ካለ በኖርዌይ ጥገኝነት የመጠየቅ መብትዎ የተጠበቀ ነው::





አንድ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የሚወስደው ጊዜ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ይለያያል:: ረጅም ጊዜ ከወሰደ ዩዲአይ የሰጡት መረጃ ትክክል መሆን አለመሆኑን እየመረመረ ሊሆን ይችላል::

ምክንያት ለምሳሌ ግብረሰዶማዊ በመሆናቸው ምክንያት የተሰደዱ ሰዎችም ጥገኝነት ሊሰጣቸው ይችላል:: የስደተኞችን ሁኔታ በተመለከተ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስምምነት ሌሎች ዝርዝሮችን አካትቷል::

የአገርዎ ባለሥልጣናት ስደቱን ከሚያደርስብዎ ወገን ከለላ እንዲያገኙ ሊረዱዎት የሚችሉ ከሆነ በኖርዌይ ጥገኝነት ለማግኘት ብቁ አይሆኑም:: ትውልድ አገራቸው ውስጥም ሆነው ቦታ ብቻ በመለወጥ ከችግሩ ሊላቀቁ ለሚችሉም ሰዎች ቢሆን ጥገኝነት መስጠት የተለመደ ነገር አይደለም::

## ከለላ

የደረሰብዎ ስደት የፖለቲካ ጥገኝነት እንዲሰጥዎ የሚያበቃ ሆኖ በማይገኝበት ሁኔታም ቢሆን በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥዎ ይችላል:: ይህ ሊሆን የሚችለው በትውልድ አገርዎ የሚካሄድ ጦርነት ሲኖር ወይም ሰብዓዊነት ለጎደለው ድርጊት ሊጋለጡ የሚችሉበት ሁኔታ ሲኖር ነው:: ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ ዩዲአይ በኖርዌይ መኖርዎን እንዲቀጥሉ ማድረግ የሚቻልበት መንገድ መኖሩን ለማረጋገጥ ይጥራል::

## የሰብዓዊነት ምክንያቶች

በአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች እርስዎ ወይም ልጆችዎ በከባድ ሕመም የሚሰቃዩ ከሆነና የዚህ ሕመም ሕክምና በአገርዎ የማይሰጥ ከሆነ በኖርዌይ እንዲቆዩ ሊፈቀድልዎ ይችላል::

## መኖሪያ

በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ሲሰጥዎ ፖሊስ ውጤቱን ያሳውቅዎታል:: ከዚያም በኖርዌይ የሚጀምሩት አዲስ ሕይወት ዝግጅት ይጀምራል:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ 7 ላይ ዝርዝር ሐሳቦችን ማግኘት ይችላሉ::

## ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

አንድ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የሚወስደው ጊዜ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ይለያያል:: ረጅም ጊዜ ከወሰደ ዩዲአይ የሰጡት መረጃ ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን እየመረመረ ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ዩዲአይ በወቅቱ በትውልድ አገርዎ ያለውን ሁኔታ እያጣራ ሊሆን ይችላል::

ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ:: ያቀረቡት ይግባኝ በኢሚግሬሽን ይግባኝ ቦርድ (UNE) ይታያል:: ዩኤንኢ አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ በአብዛኛው እስከ 10 ወር ድረስ ይወስድበታል::

## ዩዲአይ ማመልከቻዎችን ላለመቀበል ሲወስን

ዩዲአይ ለጥገኝነት ያቀረቡትን ማመልከቻ ሳይቀበለው ከቀረ በዚህ ጉዳይ የሚረዳዎ ጠበቃ ይሰይምልዎታል:: ዩዲአይ ተቀባይነት ያላገኘውን የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ለጠበቃዎ ይልካል:: ጠበቃውም ማመልከቻዎ ውድቅ መደረጉንና ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት ምን እንደሆነ ያስረዳዎታል:: በቋንቋ የማትግባቡ ከሆነ ጠበቃው አስተርጓሚ ያዘጋጃል::







ዩዲአይ ማመልከቻውን ውድቅ ባደረገበት ውሳኔ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብትዎ የተጠበቀ ነው:: ጠበቃዎ የዩዲአይ ውሳኔ ይፋ ከሆነ በኋላ ባሉት ሦስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ለዩዲአይ ማስገባት ይኖርበታል::

ጠበቃው ይግባኙን በማዘጋጀት ይረዳዎታል:: ይግባኙንም አቅርበው ዩዲአይ ማመልከቻውን ውድቅ በማድረጉ ከጸና ጉዳይዎ ለመጨረሻ ውሳኔ ወደ ኢሚግሬሽን ይግባኝ ቦድር (UNE) ይመራል:: ዩኤንኢ የኢሚግሬሽን ይግባኝ ጥያቄዎችን የሚያይ ራሱን የቻለ አካል ነው::

ጠበቃዎ ይግባኝዎን እያዘጋጀ እግረ መንገዱንም ይግባኝዎ እስኪታይ ድረስ በኖርዌይ እንዲቆዩ ይፈቀድልዎ ዘንድ ጥያቄ ያቀርባል:: ዩዲአይ ይግባኝዎ እስኪታይ በኖርዌይ መቆየት ይችሉ እንደሆነና እንዳልሆነ ይወስናል:: በመሆኑም የመጨረሻውን ውሳኔ ሳያገኙ ከኖርዌይ እንዲወጡም ሊጠየቁ ይችላሉ::

## ዩኤንኢ ማመልከቻዎን ላለመቀበል ሲወስን

ዩኤንኢም ማመልከቻዎን ውድቅ ካደረገው በአብዛኛው በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከአገር እንዲወጡ ይጠበቅብዎታል::

ዩኤንኢ ማመልከቻዎን ላለመቀበል ከወሰነ በፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ:: ይሁን እንጂ እንደዚህ ለማድረግ ከወሰኑ የሕግ ክርክር ወጪዎችዎን ራስዎ መሸፈን ይኖርብዎታል:: ፍድር ቤቱ ዩኤንኢ ጉዳዩን እንደገና ያየው ዘንድ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፍልዎ (የይታይልኝ አቤቱታ) መጠየቅ ይችላሉ:: በአብዛኛው ዩኤንኢ ጉዳይዎን እንደገና እስኪያየው ድረስ ኖርዌይ ውስጥ እንዲቆዩ አይፈቀድልዎትም::

## ወደ አገርዎ መመለስ

የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ ከአገሪቱ መውጣት ይኖርብዎታል:: ዓለም አቀፍ የማይግሬሽን ድርጅት (IOM) ወደ አገርዎ በሚያደርጉት የመልስ ጉዞ እንዲያግዝዎ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ:: በዓለም አቀፉ የማይግሬሽን ድርጅት አማካኝነት ወደ አገርዎ የሚመለሱ ከሆነ ድርጅቱ የጉዞ ወጪዎን ከመሸፈን በተጨማሪ ሌሎች ተግባራዊ እገዛዎችን ያደርግልዎታል:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ወደ አገር መመለስ የሚል ርዕስ ባለው በምዕራፍ 6 ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት ይችላሉ::

የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ ከአገሪቱ መውጣት ይኖርብዎታል:: ዓለም አቀፍ የማይግሬሽን ድርጅት (IOM) ወደ አገርዎ በሚያደርጉት የመልስ ጉዞ እንዲያግዝዎ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ::










**ኖርዌይ ከመምጣትዎ በፊት ለደህንነትዎ በማያሰጋ ሌላ አገር ይኖሩ ከነበረ ለጥገኝነት ያረቡት ጥያቄ በዚያ አገር ይታይልዎታል፡፡**

## ልጆች

ከ18 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸውና ከወላጆቻቸው ጋር ሆነው የጥገኝነት ጥያቄ የሚያቀርቡ ልጆች ጉዳይ የሚታየው በወላጆቻቸው ማመልከቻ ይሆናል፡፡ ወላጆች ዩዲአይ ልጆቻቸውን እንዲጠይቃቸው የማይፈልጉ ከሆነ ይህንኑ መናገር ይችላሉ፡፡ ዩዲአይ ቤተሰቡ ያቀረበውን የጥገኝነት ጥያቄ ሲመረምር የልጆቹ ሁኔታ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

ወላጆች በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጣቸው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችም አብረው እንዲቆዩ ይፈቀድላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የወላጆች ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገም የልጆቹም ሁኔታ የተለየ አይሆንም፡፡ ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ ራሱን ችሎ ይታያል፡፡

## ለደህንነትዎ አስተማማኝ ወደሆነ ሌላ አገር መዛወር

ኖርዌይ ከመምጣትዎ በፊት ለደህንነትዎ በማያሰጋ ሌላ አገር ይኖሩ ከነበረ ወይም ለደህንነትዎ ስጋት ከማይሆን ሌላ አገር ቪዛ ካገኙ ለጥገኝነት ያቀረቡት ጥያቄ በዚያ አገር ይታይልዎታል፡፡ በመሆኑም ወደዚያ አገር ሊላኩ ይችላሉ፡፡ ይህ የዱብሊን አሠራር በመባል ይታወቃል፡፡ የአውሮፓ ሕብረት የሆኑ ሁሉም አገራት እንዲሁም ኖርዌይና አይስላንድ የዚህ ፕሮግራም አካል ናቸው፡፡

የእርስዎ ጉዳይ የዱብሊን ጉዳይ ከሆነ የግል ሐተታ ቅጽ ይሞሉና ቃለ መጠይቅ ይደረግልዎታል፡፡ ሆኖም ለጥገኝነት ያቀረቡትን ጥያቄ የሚያዩት የኖርዌይ ባለሥልጣናት አይሆኑም፡፡ ውሳኔውን ሲጠብቁም በኖርዌይ እንዲሠሩ አይፈቀድልዎትም፡፡







## የጥገኝነት ማመልከቻዎ በሚታይበት ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች

### 1. ወንጀል

በኖርዌይ በጥገኝነት ጠያቂነት ሳሉ ሕግ ተላልፈው ቢገኙ ዩዲአይ ማመልከቻዎን በፍጥነት ያየዋል፡፡ ማመልከቻዎ ውድቅ ከሆነ ወዲያውኑ ከአገር እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ኖርዌይም ሆነ ወደ በርካታ የአውሮፓ ሕብረት አገራት መግባት አይችሉም፡፡

### 2. በጥገኝነት ጥያቄ ቃለ መጠይቁ ወቅት ያልቀረበ ተጨማሪ መረጃ

የጥገኝነት ማመልከቻው ቃለ መጠይቅ ከተደረገልዎ በኋላ ለማመልከቻዎ የሚረዳ ተጨማሪ ጠቃሚ መረጃ እንዳለዎት ከተሰማዎ በተቻለ ፍጥነት ለዩዲአይ ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡ እንዲህ ያለውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት የማሳወቅ መብትም ሃላፊነትም አለብዎት፡፡ የተጠራጠሩት ነገር ካለ ባረፉበት የመቀበያ ማዕከል ያሉትን ሠራተኞች ያነጋግሩ፡፡

### ጊዜያዊ የሥራ ፈቃድ

በኖርዌይ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ያቀረቡ ሰዎች በአንዳንድ ሁኔታዎች ውሳኔ እስኪሰጣቸው ድረስ ጊዜያዊ የሥራ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ውሳኔውን እየተጠባበቁ ሳሉ ጊዜያዊ የሥራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው በርከት ያሉ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በመቀበያ ማዕከሉ ያሉትን ሠራተኞች ይጠይቁ፡፡

### ለተጨማሪ መረጃ፥-

www.udi.no
www.noas.org
www.une.no







“ጤናዎን መንከባከብ በመቀበያ ማዕከሉ የሚኖርዎትን ቆይታ ይበልጥ የተመቸ ያደርግልዎታል”



ምዕራፍ 2

# ጤና

**ጥሩ ጤና ለማንኛውም ሰው ቢሆን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሊያገኙት ስለሚችሉት የጤና እርዳታ መረጃ የሚያገኙ ሲሆን የግል ጤናዎን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ የሚገልጹ ሐሳቦችም ሰፍረዋል::**

ጤናዎ መታወኩ የጥገኝነት ጥያቄዎ ተቀባይነት እንዳያገኝ እንቅፋት ሊሆን አይችልም:: በመሆኑም አንድ ዓይነት ከባድ ሕመም ወይም የጤና እክል ካለብዎ በግልጽ ሊናገሩ ይገባል:: በኖርዌይ ሕክምና ሊሰጥዎ ይችላል:: ጤናዎን ማሻሻል የሚችሉበትን እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ::

በኖርዌይ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች በሙሉ የታካሚዎቻቸውን ገበና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው:: ይህም ማለት የእርስዎን ፈቃድ ካላገኙ በቀር ስለ እርስዎ የጤና ሁኔታ ለማንም ሰው እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም ማለት ነው:: ሌላው ቀርቶ ስምዎን ወይም ታካሚ መሆንዎን ለሌላ ሰው እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም::

## አስተርጓሚ ያስፈልግዎታል?

የሚባለውን ነገር ስለመረዳትዎ እርግጠኛ ካልሆኑ የአስተርጓሚ እርዳታ የመጠየቅ መብትዎ የተጠበቀ ነው:: የጤና ባለሙያዎቹ አስፈላጊ እንደሆነ ከተረዱ አስተርጓሚ የማምጣት ኃላፊነት አለባቸው:: አንዳንድ ጊዜ በስልክ ያስተረጉማሉ:: አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ከሐኪም ጋር ያለዎት ቀጠሮ ከመድረሱ በፊት አስቀድመው ማሳወቅ ይኖርብዎታል:: አንድ አስተርጓሚ ለማግኘት ጥቂት ቀናት ሊፈጅ ይችላል:: ሁሉም አስተርጓሚዎች ምሥጢር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው::

## በሰዓቱ መድረስ

ከአንድ የጤና ባለሙያ ጋር ቀጠሮ ከተያዘልዎት በተባለበት ሰዓት መድረስዎ በጣም አስፈላጊ ነው:: መምጣት የማይችሉ ወይም የሚዘገዩ ከሆነ ይህንኑ ማሳወቅ ይኖርብዎታል:: ይህንን ሳያሳውቁ ከቀሩ ቀጠሮው ስለሚያመልጥዎ ሌላ አዲስ ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልግዎታል:: እንዲሁም ላሳለፉት ቀጠሮ መክፈል ይኖርብዎታል የሚል ደንብም አለ::

## አጣዳፊ ሕመም/ከባድ ጉዳት

አጣዳፊ ሕመም ከያዘዎ ወይም ደግሞ ከባድ ጉዳት ከደረሰብዎ ለመቀበያ ማዕከሉ ሠራተኞች ማሳወቅ እና/ወይም በአካባቢዎ ከሚገኘው ሆስፒታል ጋር መገናኘት ይኖርብዎታል:: ለሁለቱም ማሳወቅ ካልቻሉ የሕክምና እርዳታ እንዲደረግልዎ ይረዳዎ ዘንድ ሌላ ሰው ሊጠይቁ ይችላሉ:: አምቡላንስ ካስፈለገዎ 113 ሊደውሉ ይችላሉ::

በኖርዌይ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች በሙሉ የታካሚዎቻቸውን ገበና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው:: ይህም ማለት የእርስዎን ፈቃድ ካላገኙ በቀር ስለ እርስዎ የጤና ሁኔታ ለማንም ሰው እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም ማለት ነው::







> ብዙ ሰዎች ይበሳጫሉ፡፡ ብዙ ሰዎች የኪሳራና የብቸኝነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ማዘን፣ በቂ እንቅልፍ አለመተኛት እንዲሁም መበሳጨት፣ የድካም ስሜትና አለመረጋጋት ቢሰማዎ አያስገርምም፡፡ አንዳንድ ሰዎች የራስ ምታትና የማጥወልወል ስሜትም ያጋጥማቸዋል፡፡

## ሐኪም ጋር መቅረብ

ከታመሙ ወይም የጤና ችግር ካለብዎ የጤና ባለሙያ ያማክሩ:: በኖርዌይ የሚኖር ማንኛውም ሰው ሁልጊዜ የሚያክመውን ዶክተር (አጠቃላይ ሐኪም) የመምረጥ መብት አለው:: ጥገኝነት ጠያቂዎችም የአጠቃላይ ሐኪም እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው:: አጠቃላይ ሐኪሙ ዘንድ ሲቀርቡ ለሕክምና ምክሩ የተወሰነ ክፍያ መክፈል ይጠበቅብዎታል:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አጠቃላይ ሐኪምዎ ወደ ስፔሻሊስት ሐኪም ሊመራዎ ይችላል:: ልጆች እስከተወሰነ ዕድሜ ድረስ ነጻ የሕክምና እርዳታ ያገኛሉ::

## መድኃኒት

ኬሚስቱ (የመድሃኒት ቤት ማለት ነው) ማናቸውንም ዓይነት መድኃኒት ይሸጣል ፡፡ አንዳንዶቹን ምርቶች እንዲሁ ሄዶ መግዛት የሚቻል ሲሆን አንዳንዶቹን ግን ያለ ሐኪም ትዕዛዝ ማግኘት አይቻልም ፡፡ ጥቂት መድኃኒቶችን ከመደበኛ የገበያ አዳራሾችም ማግኘት ይቻላል ፡፡ ለከባድ ሕመም የሚሆኑ የተለዩ መድሃኒቶችን ማግኘት ከፈለጉ መንግሥት አብዛኛውን ወጪ ይሸፍናል ፡፡ ሐኪምዎ ‘በሰማያዊ የመድኃኒት ማዘዣ’ ይጽፍልዎና ከመድኃኒቱ መደበኛ ዋጋ የተወሰነውን ብቻ ከፍለው ማግኘት ይችላሉ ፡፡

## የአእምሮ ጤና

ዕጣ ፈንታው ሳይታወቅ ጥገኝነት ጠያቂ ሆኖ መቆየት ከባድ ሊሆን ይችላል ፡፡ የሚጠብቁበት ጊዜ ሊረዝም ይችላል ፡፡ ብዙ ሰዎች ይበሳጫሉ ፡፡ ብዙ ሰዎች የኪሳራና የብቸኝነት ስሜት ይሰማቸዋል ፡፡ ማዘን ፣ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት እንዲሁም መበሳጨት ፣ የድካም ስሜትና አለመረጋጋት ቢሰማዎ አያስገርምም ፡፡ አንዳንድ ሰዎች የራስ ምታትና የማጥወልወል ስሜትም ያጋጥማቸዋል ፡፡

የአእምሮ ጤናዎን ለማሻሻል ለራስዎ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር አለ ፡፡ ሩጫ ፣ እግር ኳስ ፣ የክብደት ልምምድ እና ጨዋታ ለአእምሮም ሆነ ለአካላዊ ጤናዎ ጠቃሚ ናቸው ፡፡ ማንበብ ፣ ማጥናት እና በማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፍም ተመሳሳይ ውጤት ይኖራቸዋል ፡፡ አንድ ግብ ላይ ለመድረስ ሐሳብዎን ሰብስበው እንዲሠሩ የሚረዳዎት ነገር ሁሉ ለእርስዎ ጠቃሚ ይሆናል ፡፡ ያላንዳች እንቅስቃሴ ቁጭ ብሎ ጣራ ጣራውን መቁጠር ጥሩ አይደለም ፡፡

በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከላት ከሚያርፉት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ የተለያየ ዓይነት ስደት ፣ ጦርነትና የዓመጽ ድርጊት አጋጥሟቸዋል ፡፡ አንዳንዶቹ ከእነዚህ ገጠመኞቻቸው የተነሳ የስነ ልቦና ችግር ያጋጥማቸዋል ፡፡ እንግዳ በሆነ አገርና ባሕል ውስጥ መኖራቸው ደግሞ እነዚህን ችግሮች ይበልጥ ሊያባብስ ይችላል ፡፡ የስነ ልቦና ችግር ካጋጠምዎና እርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆነ የሕክምና ባለሙያ ያማክሩ ፡፡







### የልጆች የአእምሮ ጤና

ልጆች ስሜታቸውን የሚረዳላቸውና የሚደግፋቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል ፡፡ በተለይ በጦርነት ውስጥ የነበሩና ግፍ የተፈጸመባቸው ልጆች ለችግር የተጋለጡ ናቸው ፡፡ የሚወዱትን ሰው በሞት ያጡና በቅርብ ሆነው ሰው ሲሞት ያዩ ልጆችም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው ፡፡ ብቻቸውን መሆን ወይም ጨለማ ውስጥ መቀመጥ ያስፈራቸዋል ወይም ደግሞ አንድ መጥፎ ነገር ይደርስብኛል የሚል ፍርሃት ያድርባቸዋል ፡፡ ልጆችዎ መጥፎ ገጠመኝ አሳልፈው ከነበረ ለመቀበያ ማዕከሉ ሠራተኞች ወይም ለሐኪም መንገርዎ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡

## በሽታን መከላከል

### የአመጋገብ ሥርዓት

ኖርዌይ ውስጥ እርስዎ ከለመዱት የምግብ ዓይነት የተለየ ምግብ ለመመገብ ይገደዳሉ ፡፡ በክረምት ወቅት የሚያጋጥመውን የፀሐይ ብርሃን እጦት ለማካካስ ቫይታሚን ዲ መውሰድ ይኖርብዎታል ፡፡ ጥሩ ጤና እንዲኖርዎት ለጤናዎ የሚረዳና የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ይኖርብዎታል ፡፡ ፍራፍሬ ፣ አትክልት ፣ አሳ ፣ ሥጋና የወተት ውጤቶችን መመገብ ጥሩ ነው ፡፡ የትኞቹ ምግቦች ለእርስዎ ጥሩ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ በመቀበያ ማዕከሉ ምክር መጠየቅ ይችላሉ ፡፡

በተለይ ልጆቹ ተገቢውን ነገር መመገባቸው በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ በመሆኑም ልጆችዎ ምን እንደሚመገቡ በቅርብ መከታተል ይኖርብዎታል ፡፡

### ንጽሕና አጠባበቅ

የመኖሪያ አካባቢዎን ንጽሕና መጠበቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ ይህ በሽታ የሚከሰትበትን አጋጣሚ ይቀንሳል ፡፡ የታመከ ሁኔታ ሊፈጠርባቸው የሚችሉ እንደ ኩሽና እና መታጠቢያ ቤት ባሉ ቦታዎች በሽታ አምጪ ተዋሕሲያን ሊፈለፈሉ ይችላሉ ፡፡ በመሆኑም እንደ እጅ መታጠቢያ ፣ የሽንት ቤት መቀመጫ ፣ የገላ መታጠቢያ ፣ የውሃ መውረጃ ያሉ እና ሌሎችም ቦታዎች ንጽሕናቸው መጠበቅ ይኖርበታል ፡፡

### የግል ንጽሕና

በሽታን ለመከላከል የግል ንጽህናን በአግባቡ መጠበቅም በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኋላ እንዲሁም ምግብ ከማዘጋጀትዎና ካዘጋጁም በኋላ ሁለቱንም እጅዎን በሳሙና መታጠብ ይኖርብዎታል ፡፡

**ልጆች ስሜታቸውን የሚረዳላቸውና የሚደግፋቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተለይ በጦርነት ውስጥ የነበሩና ግፍ የተፈጸመባቸው ልጆች ለችግር የተጋለጡ ናቸው፡፡**







**ኮንዶም ኤችአይቪን ይከላከላል፡፡ ከቫይረሱ ነጻ ስለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑት ከማንኛውም ሰው ጋር ወሲብ ሲፈጽሙ ኮንዶም ይጠቀሙ፡፡**

## የጥርስ ጤና

በጥርሶች መካከል የምግብ ቁርጥራጮችና ባክቴሪያዎች ይጠራቀማሉ ፡፡ የጥርስ መበላሸትን ለማስቀረት ጥርሳችንን በየዕለቱ በጥርስ ብሩሽና በጥርስ ሳሙና ማጽዳት ይኖርብናል ፡፡ የልጆችም ጥርስ እንዲሁ በጥንቃቄ መጽዳት አለበት ፡፡ ልጆችዎ የጥርሳቸውን ንጽሕና መጠበቅ እንዲችሉ ያስተምሯቸው ፡፡ የጥርስ ሕክምና ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ነገር ነው ፡፡

## የአባለዘር ጤና

### በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች

ማናቸውም በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች አንድን ሰው የሚይዙት በወሲባዊ ግንኙነት ነው ፡፡ በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችለው ብቸኛ የወሊድ መከላከያ ዘዴ የወንድና የሴት ኮንዶም ነው ፡፡ በአብዛኛዎቹ የገበያ አዳራሾች እንዲሁም በየመድኃኒት ቤቶች ውስጥ ኮንዶም ማግኘት ይችላሉ ፡፡ የሴት ኮንዶሞች የሚገኙት በመድኃኒት ቤቶች ውስጥ ነው ፡፡

በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን በነጻ የመመርመርና የመታከም መብት አለዎት ፡፡ በጾታ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች መካከል እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ኤችአይቪ ፣ ጨብጥ ፣ ቂጥኝ ፣ ባምቡሌ ፣ እና ከርክር ይገኙበታል ፡፡

ተጨማሪ ነገር ማወቅ ከፈለጉ ያረፉበትን የመቀበያ ማዕከል ሠራተኞች ወይም ሐኪምዎን ያነጋግሩ ፡፡

### ኤችአይቪ/ኤድስ

ኖርዌይ እንደደረሱ የኤችአይቪ ምርመራ የሚያደርጉበት አጋጣሚ ተሰጥትዎት ነበር ፡፡ ኤችአይቪ የሚተላለፈው ጥንቃቄ በጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት እና የሌላ ሰው ደም በመውሰድ ነው ፡፡ በተጨማሪም የእናት ጡት በመጥባትም ኤችአይቪ ሊተላለፍ ይችላል ፡፡

ኮንዶም ኤችአይቪን ይከላከላል ፡፡ ከቫይረሱ ነጻ ስለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑት ከማንኛውም ሰው ጋር ወሲብ ሲፈጽሙ ኮንዶም ይጠቀሙ ፡፡

ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት የዕለት ተዕለት ግንኙነት ምክንያት ኤችአይቪ አይዝዎትም ፡፡ ኤችአይቪ ኤድስ ካለብዎት ሕክምና የማግኘት መብትዎ የተጠበቀ ነው ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ያረፉበትን የመቀበያ ማዕከል ሠራተኞች ወይም ሐኪምዎን ያነጋግሩ ፡፡

### የሴቶች ግርዛት

የሴቶች ግርዛት በአንዳንድ ባሕሎች ዘንድ የተለመደ ነገር ነው ፡፡ በኖርዌይ ሴቶችን መግረዝ በጥብቅ የተከለከለ ነው ፡፡ ሴቶችን መግረዝ የጾታ ብልትን እንደመተልተል ይቆጠራል ፡፡ ኖርዌይ ውስጥ ብልትን በመተልተል ተግባር የተሳተፈ አሊያም ተግባሩን በማስፈጸም የተባበረ ሰው እስከ ስምንት ዓመት የሚደርስ እስራት ይፈረድበታል ፡፡ ተግባሩ የተፈጸመው ከኖርዌይ ውጭ ቢሆንም ሕጉ ኖርዌይ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ፡፡







ወደ ኖርዌይ ተገርዘው የሚመጡ ብዙ ሴቶች አሉ ፡፡ መገረዝ በሴቶች ላይ ብዙ ከባድ የጤና እክሎች ያስከትላል ፡፡ ከዚህ ቀደም የተገረዙ ሴቶች ካሉ የጤና ባለሙያዎች አስፈላጊውን ምክርና እገዛ ሊያደርጉላቸው ይችላሉ ፡፡

## የወሊድ መቆጣጠሪያ

የሕክምና ባለሙያዎች ጽንስን ለመከላከል ስለሚያስችሉዎት የተለያዩ አማራጭ ዘዴዎች ማብራሪያ ሊሰጡዎ ይችላሉ ፡፡ ለወንዶች በጣም የተለመደው የወሊድ መከላከያ ዘዴ ኮንዶም ነው ፡፡ ሴቶች ብዙ አማራጭ ይኖራቸዋል ፡፡ ለምሳሌ ያህል ፣ የወሊድ ቆጣጠሪያ እንክብል ፣ መርፌ እና ፕላስተር እንዲሁም ኮይል መጠቀም ይችላሉ ፡፡ ለእርስዎና ለሁኔታዎ ይበልጥ ተስማሚ የሆነው የትኛው እንደሆነ ለመወሰን የሕክምና ባለሙያ ያማክሩ ፡፡

## ውርጃ

ኖርዌይ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ 12 ሳምንታት ውስጥ ጽንሱን ማስወጣትና አለማስወጣት ለሴቷ የተተወ ውሳኔ ነው ፡፡ የሐኪም ፣ የቄስ ፣ የኢማም ወይም የሌላ ማንኛውም ሰው ስምምነት አያስፈልጋትም ፡፡ ባሏ የሽሉ አባት ቢሆንም እንኳ በዚህ ጉዳይ ላይ የመወሰን መብት የለውም ፡፡

ሴትዮዋ ሽሉን ማስወረድ የምትፈልግ ከሆነ ሐኪም ወይም አዋላጅ ማማከር ይኖርባታል ፡፡ አንዲት ሴት ከአስራ ሁለተኛው ሳምንት በኋላ ለማስወረድ ከፈለገች በቅርብ በሚገኝ ሆስፒታል ያለን የሐኪሞች ቡድን ስምምነት ማግኘት ይኖርባታል ፡፡ አዋላጇ ወይም ዶክተሯ በማመልከቻው ረገድ እርሷን የመርዳት ግዴታ አለባቸው ፡፡

## የቅድመ ወሊድ ሕክምና

ነፍሰ ጡር ከሆኑ በየጊዜው የቅድመ ወሊድ ምርመራ ማድረግ ይኖርብዎታል ፡፡ መሄድ የሚፈልጉት አዋላጅ ጋር ወይም ሐኪም ጋር አለዚያም ወደ ሕጻናትና የልጆች ክሊኒክ ጋር ፣ ውሳኔው ለእርስዎ የተተወ ነው ፡፡ አዋላጆችም ሆኑ ሐኪሞች እነዚህን ምርመራዎች ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና አላቸው ፡፡ ከፈለጉ በቀጠሮዎ ሌላ ሰው አብሮዎት እንዲሄድ ማድረግ ይችላሉ ፡፡ በእርግዝና ወቅት ችግሮች ካጋጠሙ ሐኪምዎ ወይም አዋላጅዎ ስፔሻሊስት ሐኪም ዘንድ እንዲቀርቡ ያደርጋሉ ፡፡

አዘውትሮ የቅድመ ወሊድ ምርመራ ማድረግ በርካታ ጥቅሞች አሉት ፡፡ የእርስዎም ሆነ የጽንሱ ጤና ቁጥጥር ይደረግለታል እንዲሁም መረጃና እገዛ ያገኛሉ ፡፡ ለቅድመ ወሊድ ምርመራዎች ክፍያ አይጠየቅም ፡፡

**አንዲት ሴት ከአስራ ሁለተኛው ሳምንት በኋላ ጽንስ ለማስወረድ ከፈለገች በቅርብ በሚገኝ ሆስፒታል ካለ የሐኪሞች ቡድን ስምምነት ማግኘት ይኖርባታል፡፡**

**ለተጨማሪ መረጃ፡-**
www.trygdeetaten.no
www.fhi.no





“እያንዳንዱ ልጅ ትምህርት
የማግኘት መብት አለው“



ምዕራፍ 3

# ትምህርት

**እያንዳንዱ ልጅ ትምህርት የማግኘት መብት አለው ፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የመላክ ኃላፊነት አለባቸው ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የኖርዌይ የትምህርት ሥርዓት ምን እንደሚመስል አንዳንድ መረጃዎችን ያገኛሉ ፡፡**

## የኖርዌይ ትምህርት ቤቶች

በኖርዌይ የአስር ዓመት ትምህርት ግዴታ ነው ፡፡ ይህም ማለት ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክና የቤት ሥራቸውን መሥራታቸውን መከታተል ይኖርባቸዋል ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃና መለሰስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው ያለ ክፍያ ሲሆን የልጆቹን የትምህርት መጽሐፍት ወጪ የሚሸፍነው የአካባቢው አስተዳደር ነው ፡፡ ልጆች ስድስት ዓመት በሞላቸው ዓመት ነሐሴ ወር ላይ ትምህርት ይጀምራሉ ፡፡

ልጆቹ በሁሉም ዓይነት የትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል ፡፡ ወላጆቻቸው ጥያቄ ካቀረቡ ልጆቹ ከክርስትና እውቀት እንዲሁም ከሃይማኖታዊና ከግብረገብ ትምህርት ክፍለ ጊዜ (ሲኬአርኢኢ) ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ ፡፡ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዓመት ልጆቹ በቀን የሚማሩት ከ4 እስከ 5 ሰዓት ለሚያክል ጊዜ ብቻ ይሆናል ፡፡ የልጆቹ ዕድሜ ከፍ እያለ ሲሄድ በትምህርት ላይ የሚቆዩበትም ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል ፡፡ በኖርዌይ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ ምሳቸውን በዕቃ ይዘው መምጣት ይኖርባቸዋል ፡፡ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚዘጋጅ ምግብ የለም ፡፡

ልጆች ከመጀመሪያው ዓመት ጀምሮ የቤት ሥራ ይሰጣቸዋል ፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው የቤት ሥራቸውን መሥራታቸውን የመከታተልና እንዲሰሩ የማገዝ ኃላፊነት አለባቸው ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላገኙት ውጤት ደረጃ አይሰጣቸውም ፤ ከዚያ ይልቅ አስተማሪዎቻቸው እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ለወላጆቻቸው በጽሁፍ ያሳውቃሉ ፡፡

ወንድና ሴት ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ተቀላቅለው የሚማሩ ሲሆን ሁለቱም ጾታዎች ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች ይወስዳሉ ፡፡ ብዙ ልጆች በመጀመሪያው ዓመት ትምህርታቸው በሳምንት አንድ ቀን ከቤት ውጭ የሚሰጣቸው ትምህርት ይኖራል ፡፡ ይህም ከቤት ውጭ የሚሰጥ ትምህርት በመባል ይታወቃል ፡፡ ኖርዌይ ውስጥ አብዛኛው የዓመቱ ክፍል በጣም ቀዝቃዛ ፣ ዝናባማና በረዷማ ነው ፡፡ በመሆኑም ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ የሚሞቅ ልብስ ፣ ቡትስ ጫማ እና የዝናብ ልብስ አድርገው መምጣታቸው በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ ምናልባት እንኳ ዝናብ ቢመታቸው የሚቀይሩት ልብስ ትምህርት ቤት ማስቀመጣቸው ጠቃሚ ይሆናል ፡፡

## ምዝገባ

ሁሉም ልጆች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በአቅራቢያቸው ባለው ትምህርት ቤት መመዝገብ ይኖርባቸዋል ፡፡ ብዙዎቹ ሰዎች ምዝገባ መቼ እንደሚከናወን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡ ሆኖም በየአካባቢው ታትመው በሚወጡ ጋዜጦች ላይም

**ግዴታ የሆነው ትምህርት የሚሰጠው ያለ ክፍያ ሲሆን የልጆቹን የትምህርት መጽሐፍት ወጪ የሚሸፍነው የአካባቢው አስተዳደር ነው፡፡ ተማሪዎች ስድስት ዓመት በሞላቸው ዓመት ነሐሴ ወር ላይ ትምህርት ይጀምራሉ፡፡**







**በኖርዌይ ከሦስት ወር በላይ የሚቆዩ ልጆች ኖርዌይ እንደደረሱ ትምህርት መጀመር ይኖርባቸዋል፡፡**

ማስታወቂያ ይወጣል፡፡ ልጁ አምስት ዓመት ሲሞላው ወላጆች ወደ ትምህርት ቤቱ ሄደው (በአብዛኛው መስከረም ላይ) የምዘገባውን ቅጽ መሙላት ይኖርባቸዋል፡፡

ልጆች በኖርዌይ ከሦስት ወር በላይ የሚቆዩ ከሆነ እንደደረሱ ትምህርት መጀመር ይኖርባቸዋል፡፡

## ከትምህርት ውጭ የሚደረግ እንክብካቤ (SFO)

ሁሉም ትምህርት ቤቶች ትናንሽ ልጆች በአዋቂዎች ጥበቃ ሥር ሆነው እንዲጫወቱ የሚያደርጉበት ከትምህርት ውጭ የሚካሄድ ፕሮግራም አላቸው፡፡ ልጆቻቸው በዚህ ፕሮገራም እንዲታቀፉላቸው የሚፈልጉ ወላጆች የሚከፍሉት ወርኃዊ ክፍያ ይኖራል፡፡ የኤስኤፍኦ ፕሮግራም ተካፋይ ለሆኑ ልጆች ቀለል ያሉ ምግቦችም ጭምር ይዘጋጁላቸዋል፡፡

## ወላጆችና ትምህርት ቤት

ልጆቹን በማሳደግ ረገድ ወላጆችና ትምህርት ቤቱ ተጋግዘው ይሠራሉ፡፡ በዓመት ሁለት ጊዜ ሁሉም ወላጆች ከአስተማሪዎቹ ጋር ተገናኝተው ይነጋገራሉ፡፡ ይህ የወላጆች ስብሰባ በመባል ይጠራል፡፡

በዓመት አንድ ጊዜ አስተማሪው የእያንዳንዱን ልጅ ወላጅ በመጥራት ልጁ በትምህርት ቤት ስለሚያደርገው ለውጥ የሚነጋገር ሲሆን የወላጆችንም አስተያየት ይጠይቃል፡፡ ከእነዚህ ስብሰባዎች በፊት በዕድሜ ከፍ ያሉት ልጆች ስለ ትምህርት ቤቱ የሚወዱትንና የሚጠሉትን ነገር እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡

ወላጆች ሐሳብ ማግኘት ከፈለጉ ወይም ደግሞ ከመምህራኑ ጋር የሚወያዩባቸው ሌሎች ጉዳዮች ካሉ በማንኛውም ጊዜ ከመምህሩ ጋር ተገናኝተው ለመነጋገር ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## የቋንቋ እገዛ

የመጀመሪያ ደረጃና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆኑ ልጆች ከተለደመው የትምህርት ሥርዓት በተጨማሪ የኖርዌይን ቋንቋ እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ ተማሪዎቹ የኖርዌይን ቋንቋ መረዳት ፣ መናገር ፣ ማንበብ እና መጻፍ እንዲችሉ ይደረጋል፡፡

አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የኖርዌይን ቋንቋ የማይችሉ ልጆችን ለብቻ የሚያስተምሩበት ዝግጅት አላቸው፡፡ ተማሪዎቹ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሊማሩ ይችላሉ፡፡ ዋናው ትኩረት የኖርዌይን ቋንቋ መሠረታዊ እውቀት እንዲጨብጡ መርዳት ነው፡፡ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ደግሞ ተማሪዎቹ ቀጥታ ወደ መደበኛው የትምህርት ክፍል እንዲገቡ ያደርጋሉ፡፡ እንዲህ በሚደረግበት ጊዜ ግን ተማሪዎቹ ከፍተኛ የሆነ ተጨማሪ የቋንቋ እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡

መምህሩ የተማሪዎቹ የኖርዌይ ቋንቋ ችሎታ የተለመደውን ሥርዓተ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችል ደረጃ ላይ ደርሷል ብሎ ሲያምን ለዕድሜያቸው ወደሚመጥን ክፍል እንዲዛወሩ ያደርጋል፡፡








ወላጆች ከልጁ መምህር ጋር በመመካከር ልጁ የኖርዌይን ቋንቋ መያዝ ያለበት እንደ ዋነኛ ቋንቋው ነው ወይስ እንደ ሁለተኛ ቋንቋው የሚለውን ይወስናሉ:: ተማሪው በትምህርት ዘመኑ የኖርዌይን ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋው አድርጎ ከተማረ በኋላ  በኖርዌይ ቋንቋ ትምህርት ወደሚሰጥባቸው መደበኛ ክፍሎች ሊዛወር ይችላል::

ልጁ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማንበብና መጻፍ በሚማርበት ጊዜ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን መማሩ በጣም ጠቃሚ ነው:: ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን የሚማርበትን ጊዜ ማራዘም ይቻላል:: አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንዳንድ ትምህርቶችን እንዲማሩ ሊደረግ ይችላል:: እንደዚያ ከሆነ ተማሪው የትምህርቱ አስተማሪና የአፍ መፍቻ ቋንቋው አስተማሪ ያለበት ክፍል ውስጥ ይገባና ትምህርቱ በቋንቋው እየተተረጎመለት ይማራል::

የኖርዌይን ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ችግር ያለባቸው ልጆች በመለስተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትምህርት ሊሰጣቸው ይችላል:: በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጠው ትምህርት ከተለመዱት የትምህርት ቀናት ውጭ ወይም ተማሪው ከሚማርበት ትምህርት ቤት ውጭ ባለ ሌላ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል::

## ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ጥገኝነት ጠያቂ የሆኑ ዕድሜያቸው ከ16-18 የሆነ ልጆች ግዴታ የሆነውን የ10 ዓመት ትምህርት ካጠናቀቁ ወይም በትውልድ አገራቸው ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ካገኙ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሊመዘገቡ ይችላሉ:: ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወይም ለሌላ ከፍተኛ ትምህርት ለመብቃት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ማጠናቀቃቸው በጣም አስፈላጊ ነው::

አብዛኛውን ጊዜ ልጆቻቸው በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማሩ የመማሪያ መጽሐፍቶቻቸውን ሒሳብ የሚሸፍኑት ወላጆች ናቸው:: የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከላት ነዋሪዎች በመቀበያ ማዕከሉ አማካኝት ዩዲአይ እነዚህን መጽሐፍት ለመግዛት የሚያስችል የገንዘብ እገዛ እንዲያደርግላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ::

አንዳንድ ተማሪዎች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውም ወቅት ተጨማሪ የቋንቋ ትምህርት ሊያስፈልጋቸው ይችል ይሆናል:: በመሆኑም አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ተጨማሪ የሁለት ዓመት የኖርዌይና እንግሊዝኛ ቋንቋ ኮርስ የሚሰጡበትን ዝግጅት አድርገዋል:: ይህም ሌሎች ትምህርቶችን ማጥናት በሚያስችላቸው መንገድ የሚደረግ ነው:: ተጨማሪ መረጃ ለማግኙት የትምህርት ቤቱን አማካሪ ይጠይቁ::

**አብዛኛውን ጊዜ ልጆቻቸው በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማሩ የመማሪያ መጽሐፍታቸውን ሒሳብ የሚሸፍኑት ወላጆች ናቸው:: የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከላት ነዋሪዎች በመቀበያ ማዕከሉ አማካኝት ዩዲአይ እነዚህን መጽሐፍት ለመግዛት የሚያስችል የገንዘብ እገዛ እንዲያደርግላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ::**

ለተጨማሪ መረጃ፥-
www.ung.no
www.bip.no
www.nokut.no
www.vox.no



“የኖርዌይ ማህበራዊ ሥርዓት ዓላማ
የነዋሪዎቹን ደህንነት ማስጠበቅ ነው“



ምዕራፍ 4

# የኖርዌይ ማኅበረሰብ



በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ኖርዌይ ማኅበረሰብ ህይወት መረጃ ያገኛሉ፡፡ በእርስዎ አገር ከሚያውቁት እውነታ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት ከእነዚህ በጣም አስፈላጊ እውነታዎች ጋር መተዋወቃቸው ወሳኝ ነው፡፡

## ዲሞክራሲ

ኖርዌይ ዲሞክራሲያዊ አገር ነች፡፡ ይህም ማለት እያንዳንዱ ሰው ድምጽ በመስጠትና አገሪቷን የሚያስተዳድረውን አካል በመወሰን ረገድ ተሳትፎ ማድረግ ይችላል፡፡

የኖርዌይ ፓርላማ ስቶርቲንግ በመባል ይታወቃል፡፡ የስቶርቲንግ አባላት የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚወክሉ ናቸው፡፡ አጠቃላይ ምርጫ የሚደረገው በየአራት ዓመቱ ነው፡፡

መንግሥት በስቶርቲንጉ የሚመሠረት ነው፡፡ ኖርዌይ በንጉሣዊ ሕገ መንግሥት የምትተዳደር አገር ነች፡፡ መራሄ መንግሥቱ ንጉሡ ቢሆኑም ፖለቲካዊ ሥልጣን የላቸውም፡፡

ኖርዌይ ባለሁለት ዘርፍ አካባቢያዊ የአስተዳደር ሥርዓት አላት፡፡ የአካባቢያዊ አገራዊ ምክር ቤት እና የአካባቢውን የወረዳ ምክር ቤት አባላት ለመምረጥ ምርጫ ይካሄዳል፡፡ ከ18 ዓመት በላይ የሆነው ሁሉም የኖርዌይ ዜጋ በአጠቃላዩ ምርጫ (ለስቶርቲንግ) የመሳተፍ መብት ያለው ቢሆንም የመምረጥ ግዴታ ግን የለበትም፡፡

ከምርጫው ቀን በፊት በኖርዌይ ለሦስት ዓመታት ከኖሩ የኖርዌይ ዜግነት ባይኖርዎትም በአገራዊ ምክር ቤት እና በወረዳ ምክር ቤት ምርጫዎች ድምጽ መስጠት ይችላሉ፡፡

## ሕገ መንግሥት

ኖርዌይ ውስጥ ከሁሉ የላቀው ሕግ ሕገ መንግሥቱ ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ አገሪቱን ማን እንደሚያስተዳድርና እንዴት ማስተዳደር እንዳለበት ይወስናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ በኖርዌይ የሚኖሩትን ሰዎች መሠረታዊ የሆኑ መብቶች ይዘረዝራል፡፡

## የሥልጣን ክፍፍል

ኖርዌይ ውስጥ ሥልጣን ለሦስት ወገኖች የተከፋፈለ ነው፡፡ እነርሱም ሕግ አውጭው ስቶርቲንግ (ፓርላማ) ፣ ሕጉን የሚተረጉመው መንግሥት እና የሚያስፈጽመው የፍትሕ አካል (ፍርድ ቤት) ናቸው፡፡ ሥልጣን ለሦስት አካላት መከፋፈሉ አንዳቸው የሌላውን የሥልጣን ሚዛን እንዲያስጠብቁና የትኛውም የመንግሥት አካል ለራሱ ጥቅም ስልጣኑን አላግባብ እንዳይጠቀምበት ለማድረግ ያስችላል፡፡

**ሕጎችና ደንቦች የኖርዌይ ነዋሪዎች መብት መከበሩን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ሕጉ በኖርዌይ የሚኖረውን የእያንዳንዱን ሰው ግዴታ ይዘረዝራል፡፡ ማንም ሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሳይታይ አይታሠርም፡፡**







## ሕገ ደንብ

ማንኛውም ሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሳይታይለት አይታሠርም፡፡ ሕግና ደንቡ ማንኛውም የኖርዌይ ነዋሪ መብቱ እንዳይጣስ ለማድረግ የቆሙ ናቸው፡፡ ሕጉ የእያንዳንዱን የኖርዌይ ነዋሪ ግዴታም ይዘረዝራል፡፡ ሰዎችን የመቅጣት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡ ይህ ሕገ ደንብ ይባላል፡፡

## የመናገር ነጻነት

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመናገር ነጻነት አብይ ድርሻ አለው፡፡ የመናገር ነጻነት ማለት ማንም ሰው በሚናገረው ወይም በሚያስበው ነገር ምክንያት አይከሰስም ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በማኅበረሰብ ውስጥ ስላሉት ሁኔታዎች የሚሰማውን በነጻነት መግለጽ ይችላል፡፡

ኖርዌይ ውስጥ ከአንድ መቶ የሚበልጡ ጋዜጦች እየታተሙ ይወጣሉ፡፡ በርካታ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ጣቢያዎችም አሉ፡፡ ጋዜጠኞች ብዙውን ጊዜ መንግስትን ፣ ሥልጣን ያላቸውን ሌሎች ሕዝባዊ አካላትና ሰዎች ይተቻሉ፡፡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## ሃይማኖታዊ ነጻነት

የኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን ኖርዌይ ውስጥ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም እያንዳንዱ ሰው የራሱን ሃይማኖታዊ አቋም የማራመድ መብቱ የጠበቀ ነው፡፡ ሃይማኖታዊ መብት ሲባል ሃይማኖታዊ ያለመሆንንም መብት ይጨምራል፡፡ ሃይማኖት በተወሰነ መጠን በኖርዌይ የፖለቲካና ማኅበራዊ ኑሮ ላይ ተጽዕኖ አለው፡፡ አብዛኞቹ ሰዎች ሃይማኖትና እምነት የግል ጉዳይ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

## እኩልነትና እኩል መብት

ኖርዌይ ውስጥ በጾታ ፣ በዘር ፣ በሃይማኖት ወይም በወሲባዊ አቋም ምክንያት በሌላ ሰው ላይ መድልዎ መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡ ወንድና ሴት እኩል በመሆናቸው በማንኛውም የማኅበረሰቡ ሕይወት ውስጥ እኩል ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

የጾታ እኩልነት ማለት በቤትም ሆነ በሥራ ቦታ ወይም በፖለቲካዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ወንድ እና ሴት እኩል አጋጣሚ ፣ መብት እና ግዴታ አላቸው ማለት ነው፡፡

## ዌልፌር ስቴት

የኖርዌይ መንግሥት የሚራብ ወይም ትምህርት ፣ ሕክምና ፣ ልብስ ወይም መጠለያ አጥቶ የሚቸገር ሰው እንዳይኖር ይከታተላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሥርዓት ዌልፌር ስቴት ይባላል፡፡

የአካባቢውና የማዕከላዊ መንግሥት ባለ ሥልጣናት ለትምህርት ቤቶች ፣ ለሆስፒታሎች ፣ ለመንገድ ግንባታ ፣ ለጡረታ ፣ ለማኅበራዊ አገልግሎቶች እና ለሌሎች ዓላማዎች የሚውል ገንዘብ ይመድባሉ፡፡

ገንዘቡ የሚገኘው የአገሪቱ ነዋሪዎች ከሚከፍሉት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ቀረጥ ነው፡፡ አንድ ነገር በገዙ ቁጥር ከሚከፍሉት ገንዘብ የተወሰነው ለመንግሥት ገቢ የሚሆን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንግሥት ከነዳጅ ምርት እና ከሌሎችም የንግድ እንቅስቃሴዎች ገቢ ያገኛል፡፡ ቁልፍ ሚና ያላቸው በርካታ ኩባንያዎች በኖርዌይ መንግሥት ይተዳደራሉ፡፡

## ቀረጥ

በኖርዌይ የሚኖር ሁሉም ሰው ከሚያገኘው ነገር ቀረጥ ይከፍላል፡፡ ብዙ ገቢ ያላቸው ሰዎች ብዙ ግብር ሲከፍሉ ገቢያቸው አነስተኛ የሆነ ደግሞ እንደዚያው የሚከፍሉት ግብር አነስተኛ ነው፡፡ መንግስት ከቀረጥ በሚያገኘው ገቢ ተጠቅሞ የተለያዩ የማኅበራዊ ደህንነት አገልግሎቶችንና ጥቅሞችን እንድናገኝ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ፣ እርስዎ የሚኖሩበት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ፣ ልጆችዎ የሚማሩበት ትምህርት ቤት እንዲሁም ሕክምና የሚያገኙበት ሆስፒታል ሁሉ ወጪያቸው የሚሸፈነው ኖርዌይ ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው በሚከፍለው ቀረጥ ነው፡፡

ከቀረጥ የሚገኘው ገቢ ሁሉንም ሰው ለሚጠቅሙ የሕዝብ አገልግሎቶች ስለሚውል ገቢ ያለው ሰው ሁሉ ቀረጥ በመክፈል የበኩሉን ድርሻ ማበርከቱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መክፈል የሚገባዎትን ቀረጥ ሳይከፍሉ ከቀሩ ቅጣት ሊጣልብዎና ወደ እስር ቤት ሊወርዱ አሊያም የቀረጥ መቀጮ እንዲከፍሉ ሊደረግ ይችላል፡፡





ኖርዌይ ውስጥ ሥራ ለማግኘት የኖርዌይ መታወቂያ ወይም የኖርዌይ የሥራ ፈቃድ ሊኖርዎት ይገባል:: የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጠዎ የግል መለያ ቁጥር ይኖርዎታል:: በኖርዌይ በክፍያ የሚሠሩ ከሆነ የቀረጥ ካርድ ማውጣት ይኖርብዎታል:: ካርዱ ከደሞዝዎ ላይ ምን ያህል መቀረጥ እንዳለበት የሚያመለክት ይሆናል:: ካርዱን በአቅራቢያዎ ካለ የቀረጥ ቢሮ ማግኘት ይችላሉ::

ከእያንዳንዱ ቀጣሪዎ የሚያገኙት ክፍያ ከ1000 የኖርዌይ ገንዘብ NOK ያነሰ ከሆነ ከደሞዝዎ ላይ የሚቀነስ ቀረጥ አይኖርም:: በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ (ምዕራፍ 7ን ይመልከቱ::) በፕሮግራሙ ላይ በሚሳተፉበትም ጊዜ ከሚያገኙት ገንዘብ ቀረጥ መክፈል ይኖርብዎታል:: ሥራ ካገኙና ክፍያ ከተቀበሉ ላቡበት የመቀበያ ማዕከል ማሳወቅ ይኖርብዎታል:: በአቅራቢያዎ ያለው የቀረጥ ቢሮ በኖርዌይ ስለ መሥራትና ስለ ቀረጥ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል::

## የልጆች መብት

ልጆች ግልጽና ትልቅ ቦታ የሚሰጠው መብት አላቸው:: ምግብ፣ መጠለያ፣ ሕክምና፣ ልብስ እና ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው:: የፈለጉትን የማሰብና የማመን መብት ያላቸው ከመሆኑም ሌላ ማኅበረሰቡ ሊሰጣቸው የሚችለውን ከሁሉ የተሻለ ነገር የማግኘት መብት አላቸው:: ልጆች እነርሱን የሚነካ ማንኛውም ነገር ሲኖር ሐሳባቸው ሊደመጥ ይገባል:: አንድ ልጅ ለሚያቀርበው ሐሳብ የሚሰጠው ክብደት እንደ ዕድሜውና የብስለት ደረጃው የሚወሰን ይሆናል:: የኖርዌይ ባለ ሥልጣናት በኖርዌይ የሚገኙ ልጆች መብት መከበሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው:: መንግሥት ሁሉንም ልጆች ከማንኛውም ዓይነት በደል ይከላከላል::

ከወላጆቻቸው ጋር የማይኖሩ ልጆች ተጨማሪ ጥበቃና እገዛ የማግኘት መብት አላቸው:: መንግሥት ጥገኝነት የሚጠይቁ ልጆችን ይረዳል እንዲሁም ከቤተሰባቸው ጋር እንዲገናኙ ለማድረግ ይጥራል::

## የልጆች አስተዳደግ

ወላጆች የልጆቻቸውን ጥቅምና ፍላጎት በሚያሟላ መንገድ ልጆቻቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል:: ልጆች የኖርዌይ ማኅበረሰብ እንዴት እንደሚሠራ እንዲማሩ ይደረጋል:: እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶችና የእኩልነት መርህ እንዲገባቸው ይደረጋል:: ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ልጆችን በማንኛውም መንገድ መምታት ወይም በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣት መፈጸም በሕግ የተከለከለ ነው:: በልጆች ላይ አእምሮአዊ በደል መፈጸምም ሕገወጥ ድርጊት ነው::

## ልጆች እና ሥራ

ከ12 ዓመት በታች ያሉ ልጆች ተቀጥረው እንዲሠሩ አይፈቀድላቸውም:: አስራ ሦስተኛ ዓመታቸውን ካከበሩ በኋላ ግን እንደ ጋዜጣ ማድረስ ያሉ ቀላል ሥራዎችን መሥራት ይችላሉ:: ሥራው የልጆቹን ደህንነት፣ ጤና ወይም እድገት አደጋ ላይ የሚጥል ወይም ደግሞ ትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆን የለበትም::

## የልጆች የዌልፌር አገልግሎት

የልጆች የዌልፌር አገልግሎት ተግባር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ልጆችን መርዳት ነው:: የልጆች የዌልፌር አገልግሎት ኖርዌይ ውስጥ ያለ የአንድ ልጅ ደህንነት አደጋ ላይ እንደወደቀ ካመነበት ጣልቃ ሊገባ ይችላል:: አብዛኛውን ጊዜ የልጆች ዌልፌር ሠራተኞች ወላጆች ልጆቻቸውን መንከባከብ የሚችሉበትን መመሪያ ይሰጣሉ::

አብዛኛውን ጊዜ ከበድ ያሉ ጉዳዮች ሲፈጠሩ ወይም የልጆቹ ደህንነት አደጋ ላይ ሲወድቅ የልጆች ዌልፌር አገልግሎት ልጁ አሳዳጊ ዘንድ እንዲቀመጥ ወይም ወደ ልጆች መኖሪያ እንዲወሰድ ያደርጋል:: የዚህ ዓላማ ልጁ ከወላጆቹም ጋር ኖረ በልጆች ዌልፌር አገልግሎት ጥበቃ ሥር ፤ ተገቢውን እንክብካቤ ማግኘቱን ማረጋገጥ ነው:: ስለ ልጆች ዌልፌር አገልግሎት ጥያቄ ካለዎት እርስዎ ባሉበት የመቀበያ ማዕከል ያሉትን ሠራተኞች ይጠይቁ::









## የቤተሰብ ሕይወት

ኖርዌይ ውስጥ ከ18 ዓመት በላይ የሆነው ሰው ከፈለገው ሰው ጋር ለመኖር የመምረጥ መብት አለው:: ብዙ ሰዎች የሚኖሩት ብቻቸውን ነው:: አንዳንድ ሰዎች ነጠላ ወላጆች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከተመሳሳይ ጾታ አጋራቸው ጋር ይኖራሉ:: ከጓደኞቻቸው ጋር የሚኖሩም አሉ:: ጋብቻ መፈጸም ይችላሉ ወይም ደግሞ ለባለሥልጣናት በማሳወቅ ከአጋርዎ ጋር አብረው መኖር ይችላሉ:: አለዚያም እንዲሁ ዝም ብለው አብረው መኖር ይችላሉ:: ኖርዌይ ውስጥ ግብረሰዶማዊ ሰዎች ተመዝግበውም ሆነ ሳይመዘገቡ አብረው መኖር ይችላሉ::

### ለተጨማሪ መረጃ፡-

www.krisesenter.com
www.skatteetaten.no
www.bufdir.no

## ጋብቻ

ወንዶችና ሴቶች ትዳር ለመመሥረት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ መሆን ይኖርበታል:: እያንዳንዱ ሰው ማንን እንደሚያገባ የመምረጥ መብት አለው:: ኖርዌይ ውስጥ ማንም ሰው ትዳር እንዲመሠርት ሊገደድ ወይም ተጽዕኖ ሊደረግበት አይችልም:: በተጨማሪም ልጆችም ሆኑ በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች ትዳር እንዲመሠርቱ በግድ ወደ ሌላ አገር ሊላኩ አይችሉም:: ጋብቻው የተፈጸመው በግዳጅ ከሆነ ለቤተሰብ ውህደት የሚቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት አያገኝም:: በግዳጅ የተፈጸመ ጋብቻ ኖርዌይ ውስጥ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ሊሰረዝ ይችላል:: ጋብቻውን የማሰረዝ የፍርድ ሂደት የግዳጅ ጋብቻው ከተፈጸመ በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ መጀመር ይኖርበታል::

ኖርዌይ ውስጥ ከአንድ በላይ ማግባት በህግ የተከለከለ ነው:: በትዳር ላይ ትዳር መመሥረት ወይም የመጀመሪያው ትዳር በሕጋዊ መንገድ ሳይፈርስ ሌላ ማግባት ወንጀል ነው::

## ፍቺ

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እኩል የፍቺ መብት አላቸው:: አንደኛው የትዳር ጓደኛ በትዳሩ መቀጠል የማይፈልግ ከሆነ በመጀመሪያ በይፋ የመለያየት ጥያቄ (ይህ ፍቺ ከመፈጸሙ በፊት የሚኖር የይርጋ ጊዜ ነው) ማቅረብ ይኖርበታል:: ሁለቱ ሰዎች ተለያይተው አንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ አንደኛው ወገን ፍቺ መጠየቅ ይችላል:: በተለያዩበት ጊዜ ሁለቱ ሰዎች አንድ ላይ ላይኖሩ ይችላሉ:: ባልና ሚስቱ አብረው የኖሩት ከሁለት ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ተለያይተው መቆየት ሳያስፈልጋቸው ፍቺ መጠየቅ ይችላሉ:: መፋታት የፈለጉት ባልና ሚስት ልጆች ካሏቸው ለፍቺ ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት የቤተሰብ የምክር አገልግሎት ፕሮግራም ላይ መካፈል ይኖርባቸዋል::

ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው በሌላኛው ላይ ከፍተኛ በደል የፈጸመ ፣ ለመግደል የሞከረ ወይም ዓመጽ እንደሚፈጽምበት ወይም በደል እንደሚያደርስበት ያስፈራራ እንደሆነ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጋብቻው ሊሰረዝ ይችላል::

## ዓመጽ

ኖርዌይ ውስጥ በቤተሰብ አባላት ላይ ዓመጽ መፈጸም ወይም ለመፈጸም መዛት የተከለከለ ነው:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ 5 ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት ይችላሉ:: በመላው አገሪቷ 50 የሚያክሉ በቤተሰብ ውስጥ ዓመጽ ለተፈጸመባቸው ሰዎች የተዘጋጁ መጠለያዎች አሉ:: እነዚህ መጠለያዎች አካላዊ ጥቃት የተፈጸመባቸውንና ማስፈራሪያ የተሰነዘረባቸውን ሰዎች ተቀብለው ያስተናግዳሉ:: ከእነዚህ መጠለያዎች በአንደኛው ጥገኝነት ለመጠየቅ ወይም ከመጠለያዎቹ ጋር ግንኙነት ለማድረግ የሌላ ወገን ፈቃድ ማግኘት አያሻዎትም::





“የጥገኝነት ጥያቄ እንዴት እንደሚያዝ
ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው“



# የጥገኝነት ጥያቄ ሂደት ደረጃ በደረጃ



1
ኖርዌይ ሲደርሱ በጥገኝነት ጠያቂነት ፖሊስ ዘንድ ቀርበው ይመዘገባሉ፡፡



2
ወደ መሸጋገሪያ ማዕከል ይዛወራሉ፡፡



3
በኖርዌይ የኢሚግሬሽን ዳይሬክቶሬት (UDI) ቃለ መጠይቅ ይደረግልዎታል፡፡

**48**

4
መሠረት የላቸውም ተብለው የሚታሰቡ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ይታያሉ፡፡



5
ወደ ሌላ የመሸጋገሪያ ማዕከል ወይም መደበኛ የጥገኝነት ጠያቂዎች ማዕከል ይዛወራሉ፡፡



6
ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ ይታያል፡፡ እነዚህን ማመልከቻዎች ለማየት የሚያስፈልገው ጊዜ እንደ ጉዳዩ ዓይነት ይለያያል፡፡



7
ብቻቸውን የመጡ ልጆች ማመልከቻ በተቻለ ፍጥነት ይታያል፡፡

8

ውሳኔው ይነገርዎታል፡፡ የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጥዎ ለእርስዎ ማረፊያ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ማዘጋጃ ቤት የማግኘቱ ጥረት ይቀጥላል፡፡ ይሁን እንጂ ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካላገኘ ይግባኝ መጠየቅ ወይም ወደ አገርዎ መመለስ ይችላሉ፡፡

a



ወደ አንዱ የአገሪቱ ማዘጋጃ ቤት እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡

b



ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካላገኘ ውሳኔውን ይግባኝ ማለት ይችላሉ፡፡ ይግባኙን ማቅረብ የሚኖርብዎት ማመልከቻው ውድቅ መደረጉ ከተነገርዎ በኋላ ባለው ሦስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ይግባኙን በመጠየቅ ረገድ ጠበቃዎ ሊረዳዎ ይችላል፡፡



ዩዲአይ ይግባኙን ካየም በኋላ በውሳኔው ከጸና ጉዳዩ ወደ ኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ (ዩኤንኢ) ይመራል፡፡ ዩኤንኢም ባብዛኛው በ10 ወራት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡



ዩኤንኢ ይግባኙን ውድቅ ካደረገው ውሳኔው የመጨረሻ ስለሚሆን ወደ አገርዎ መመለስ ይኖርብዎታል፡፡ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ከፈለጉ ይችላሉ፣ ሆኖም ውጪውን የሚሸፍኑት ራስዎ ይሆናሉ፡፡



“ሁሉም የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎች
የሚዳኙት በተመሳሳይ ሕግ ነው“

ማመልከቻዎ እስከሚታይ ድረስ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚቆዩ ማወቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው::



“የኖርዌይን ህግጋት ተላልፈው እንዳይገኙ ስለ አገሪቱ ህጎች ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው“



ምዕራፍ 5

# ሕጉን ማወቅ



**እያንዳንዱ ሃገር ነዋሪዎቹ ሊታዘዙት የሚገባ ህግ አለው:: ይህ ደግሞ ለእያንዳንዱ ሰው ደህንነት ጠቃሚ ነው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከአንዳንዶቹ የኖርዌይ ህግጋት ጋር እንዲተዋወቁ ይደረጋል::**

በኖርዌይ ያለ እያንዳንዱ ሰው ህጋዊና ህገወጥ የሆነውን ነገር ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል:: በኖርዌይ እስከኖሩ ድረስ የኖርዌይን ህግ መታዘዝ ይጠበቅብዎታል:: አንዳንድ የኖርዌይ ህግጋት በሌሎች አገሮች ከሚሰራባቸው ህጎች የተለዩ ናቸው:: የኖርዌይን ህግ ሳያውቁ ቢያፈርሱ እንኳን በዋፋተኝነት ሊከሰሱ ይችላሉ:: በመሆኑም ጉልህ ከሆኑት ህግጋት ጋር መተዋወቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው::

በኖርዌይ ውስጥ ህግ ከሃይማኖት ወይም ከልማዳዊ ድርጊቶች የበለጠ ተፈጻሚነት አለው:: ይህም ማለት የኖርዌይ ህግ ከእርስዎ ባህል ጋር የሚቃረን ቢሆንም እንኳን ህጉን መታዘዝ አለብዎት ማለት ነው:: አንድን ህገወጥ ድርጊት ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ልማድ ነው በሚል ማስተባበል አይቻልም::

አንድ ድርጊት በኖርዌይ ውስጥ ህጋዊ ይሁን ህገወጥ እርግጠኛ ካልሆኑ ያረፉበትን የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ሠራተኞች ይጠይቁ::

እርስዎ ያረፉበት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ሰራተኞች ከመረጃ ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ ስለ ኖርዌይ ህግጋት ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ይሰጡዎታል::

## ፖሊስ

ፖሊስ ብዙ የሚያከናውናቸው ተግባራት አሉ:: ወንጀልን ይከላከላል እንዲሁም ሰላምን ያስከብራል:: በአገሪቱ የግዛት ክልል ውስጥ ያሉትን ሰዎች ከአደጋ ይጠብቃል እንዲሁም ወንጀልን ያጣራል::

## ጥገኝነት ጠያቂዎችና ወንጀል

በጥገኝነት ጠያቂነት ኖርዌይ ውስጥ እያሉ የአገሪቱን ህግ ከተላለፉ ዩዲአይ ማመልከቻዎን ባስቸኳይ ይመረምራል:: ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ በፍጥነት ከአገር እንዲወጡ ይደረጋል:: ከዚህ በኋላ ወደ ኖርዌይም ሆነ ወደ ሌሎች በርካታ የአውሮፓ አገሮች መግባት ቀላል አይሆንም::

ከጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ የሃሰት መረጃ ወይም የተጭበረበረ ሰነድ ማቅረብ ህገወጥ ድርጊት ነው:: ማመልከቻው በመጨረሻው ውሳኔ ውድቅ የተደረገባቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ አገሪቷን ለቀው መውጣት

**ህግ ከሃይማኖት ወይም ከልማዳዊ ድርጊቶች የበለጠ ተፈጻሚነት አለው:: ይህም ማለት የኖርዌይ ህግ ከባህላዊው ልማድ የሚቃረን ቢሆንም እንኳን ሁሉም ሰው ህጉን መታዘዝ አለበት ማለት ነው::**







**ህግ ተላልፈው ከተገኙ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል:: ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙና የፈጸሙት ከበድ ያለ የወንጀል ድርጊት ከሆነ በማረሚያ ቤት ለብዙ ዓመታት እንዲታሰሩ እና/ወይም ከፍተኛ መጠን ያለው መቀጮ እንዲከፍሉ ሊወሰንብዎት ይችላል::**

ይኖርባቸዋል:: ሳይወጡ ከቀሩ ግን በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሊውሉ ፣ ወህኒ ቤት ሊገቡ ወይም ከአገር እስኪወጡ ድረስ ጥበቃ ወደሚደረግበት የማቆያ ማዕከል ሊላኩ ይችላሉ::

### ቅጣት

ህግ ተላልፈው ከተገኙ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል:: ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙና የፈጸሙት ከበድ ያለ የወንጀል ድርጊት ከሆነ በማረሚያ ቤት ለብዙ ዓመታት እንዲታሰሩ እና/ወይም ከፍተኛ መጠን ያለው መቀጮ እንዲከፍሉ ሊወሰንብዎት ይችላል:: በኖርዌይ ከፍተኛው የእስር ቅጣት 21 ዓመት ነው:: ይህ ከፍተኛ የእስር ቅጣት በአንድ ሰው ላይ የሚበየነው ከአደንዛዥ እጽና ከነፍስ ግድያ ጋር በተያያዘ ከባድ የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመ ነው:: በኖርዌይ የሞት ቅጣት ፍርድ አይበየንም::

## የተለያዩ ጥፋቶች

### *መድልዎ*

*መድልዎ* ማለት ሌላውን ሰው በጾታው ፣ በዜግነቱ ፣ በዘሩ ፣ በሃይማኖቱ ፣ በቆዳ ቀለሙ ፣ ባለበት የአካል ጉዳት ፣ ወይም በወሲባዊ አቋሙ ምክንያት ከሌሎች ያነሰ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ማለት ነው::

በጎሳዎ ምክንያት ከሌሎች ያነሱ እንደሆኑ ተደርገው ከተቆጠሩ የዘር መድልዎ ተፈጽሞብዎታል ማለት ነው:: ይህ በኖርዌይ ውስጥ ህገወጥ ድርጊት ቢሆንም በሱቆች ፣ በስራ ቦታ ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ በሌሎች አጋጣሚዎች ሊያጋጥም የሚችል ነገር ነው:: ባረፉበት የጥገኝነት መቀበያ ማዕከል ሳይቀር መድልዎ ሊያጋጥምዎ ይችላል::

መድልዎ እንደተፈጸመብዎ በመግለጽ ይህንን ድርጊት በተመለከተ እርምጃ የመውሰድ መብትዎ የተጠበቀ ነው:: የዘረኝነት ወይም የሌላ ከበድ ያለ መድልዎ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ የዚህ ድርጊት ፈጻሚዎች ፍርድ ፊት ሊቀርቡ ይችላሉ:: ባረፉበት የጥገኛ መቀበያ ማዕከል ያሉት ሰራተኞችም ከመረጃ ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጡዎታል::

### ዓመጽና የዓመጽ ስጋት

ዓመጽና በሌላ ሰው ላይ የአካል ጉዳት ማድረስ በኖርዌይ ህገወጥ ድርጊት ነው:: ይህ የቤተሰብ አባላትን ይጨምራል:: በሌላ ሰው ላይ የዓመጽ ድርጊት ለመፈጸም ማስፈራራትም ህገወጥ ድርጊት ነው:: ህጉ በተለይ በሴቶችና በህጻናት ላይ የሚፈጸምን ዓመጽ በተመለከተ ያለው አቋም ጥብቅ ነው:: በቤተሰብ መካከልም ሆነ ከቤተሰብ ውጪ የሚፈጸም ማንኛውም ዓመፅ ህገወጥ ድርጊት ነው::

የግዳጅ ወሲብ / ወሲባዊ በደል

ኖርዌይ ውስጥ የግዳጅ ወሲብ መፈጸም ከባድ ወንጀል ነው:: ይህ በትዳር መካከል የሚፈጸመውንም የግዳጅ ወሲብ ይጨምራል::








የጥቃቱ ሰለባ የሆነው ሰው የነበረው አለባበስም ሆነ ያሳየው የነበረው ጠባይ የግዳጅ ወሲቡን ጥፋት አያቀልለውም:: ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ አንድ የግዳጅ ወሲብ ፈጻሚ ሰው ወህኒ ቤት እንዲወርድ ይደረጋል::

## የስምምነት ዕድሜ ገደብ

ኖርዌይ ውስጥ ከ16 ዓመት በታች ካለው ሰው ጋር የጾታ ግንኙነት መፈጸም (ሁለቱም ሰዎች በስምምነት ቢያደርጉትም እንኳን) ህገወጥ ድርጊት ነው:: የወሲብ ተጓዳኙ ዕድሜ ከ16 ዓመት በላይ መሆኑን ማረጋገጥ የእያንዳንዱ ሰው ሃላፊነት ነው::

## በዘመዳሞች መካከል የሚፈጸም ወሲብ

በቤተሰብ አባላት መካከል (ወላጅ ፣ ልጆች ፣ እህትና ወንድም ፣ አያት ወዘተ) የሚፈጸም ወሲብ ኖርዌይ ውስጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው::

## የጾታ ብልትን መተልተል

ኖርዌይ ውስጥ የሴቶች ግርዛት በጥብቅ የተከለከለ ድርጊት ነው:: “ሱና”ን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት የሴቶች ግርዛት የጾታ ብልትን እንደመተልተል ይቆጠራል:: የልጃገረዶችን ወይም የሴቶችን የጾታ ብልት በመተልተል ተግባር እንዲሳተፍ ሌላውን ማስገደድ ፣ ለመሳተፍ መስማማት ወይም መሳተፍ ህገወጥ ድርጊት ይሆናል:: የጾታ ብልትን መተልተል እስከ 8 ዓመት በሚደርስ እስር የሚያስቀጣ ተግባር ነው:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ 2 ላይ ተጨማሪ ሃሳብ ማግኘት ይችላሉ:: እርስዎ ባረፉበት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ያሉት ሰራተኞች ይህንን ህግ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ::

## በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች

በጾታ ግንኙነት የሚተላለፍ ህመም እንዳለብዎት እያወቁ በበሽታው ሌሎችን ሰዎች ካስያዙ ፍርድ ፊት ሊቀርቡ ይችላሉ:: በጾታ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ ይኖርብኛል የሚል ጥርጣሬ ካለዎት ሀኪም ማማከር ይኖርብዎታል:: ሃኪሞች የታካሚዎቻቸውን ገመና የመደበቅ ግዴታ አለባቸው:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ 2 ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያ ያገኛሉ::

## በሃይል የሚፈጸም ጋብቻ

በኖርዌይ የሚኖር ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው ማንን እንደሚያገባ የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው:: ይህም ማለት ማንኛውም በኖርዌይ የሚኖር ሰው ያለ ፈቃዱ በኖርዌይ ውስጥም ሆነ ከኖርዌይ ውጪ ከሚኖር ሰው ጋር ጋብቻ እንዲፈጽም አይገደድም:: ሁሉም ሰው ፍቺ ለመፈጸም የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው::

**መድልዎ ኖርዌይ ውስጥ ህገወጥ ድርጊት ነው:: የዘረኝነት ወይም የሌላ ከበድ ያለ መድልዎ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ የዚህ ድርጊት ፈጻሚዎች ፍርድ ፊት ሊቀርቡ ይችላሉ::**








**ልጆች በሃይለኛ ምት፣ በእርግጫ ወይም በሌላ በማንኛውም የሃይል ድርጊት ሊቀጡ አይገባም:: በልጆች ላይ የሚፈጸም ሁሉም ዓይነት አካላዊና ስነ ልቦናዊ ቅጣት ህገወጥ ሲሆን ይህ ጥፋት የእስር ፍርድ ሊያስከትል ይችላል::**

በብዙ ሃይማኖቶች ዘንድ ጋብቻ ቅዱስ ነገር ነው:: የሆነ ሆኖ በሌሎች ባህሎች ወይም ሃይማኖታዊ ልማዶች የሚሰራባቸው የተለዩ ደንቦች ቢኖሩም ህጉ መከበር ይኖርበታል:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ 4 ላይ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ::

## በልጆች ላይ የሚፈጸም በደል

ልጆች በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጪ በሃይለኛ ምት ፣ በእርግጫ ወይም በሌላ በማንኛውም የሃይል ድርጊት ሊቀጡ አይገባም:: በልጆች ላይ የሚፈጸም ማንኛውም አካላዊም ሆነ ስነ ልቦናዊ ቅጣት ህገወጥ ሲሆን ፈጻሚዎቹም ህግ ፊት ይቀርባሉ:: በልጆች ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ በደል በጥብቅ የተከለከለ ሲሆን እንዲህ ያለው ድርጊት በረጅም ዘመን እስር ያስቀጣል::

የቻይልድ ዌልፌር ሰርቪስ የልጁ ደህንነት አደጋ ላይ እንደወደቀ ካመነበት ጣልቃ ይገባል:: ደህንነቱ አደጋ ላይ የወደቀ ልጅ የሚያውቁ ከሆነ ለቻይልድ ዌልፌር ሰርቪስ ሊጠቁሙ ይችላሉ:: ብዙውን ጊዜ የቻይልድ ዌልፌር ሰራተኞች ወላጆች ልጆቻቸውን መንከባከብ የሚችሉበትን መመሪያ ይሰጣሉ:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ 4 ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ::

## የጦር መሳሪያ

ራስን ለመከላከል ታስቦም ቢሆን የጦር መሳሪያ ፣ ቢላዋ ወይም ሌላ አይነት መሳሪያ መታጠቅ ህገወጥ ድርጊት ነው:: ይህ ተመሳስለው የተሰሩ የጦር መሳሪያዎችን ፣ መጫወቻዎችን ፣ ኤርሶፍት ጋኖችን እና ሌሎች በመሳሪያ መልክ የተዘጋጁ ቁሳቁሶችንም ይጨምራል:: ከኖርዌይ ባለስልጣናት የተለየ ፈቃድ ሳያገኙ የጦር መሳሪያ መግዛትም ሆነ መሸጥ ህገወጥ ድርጊት ነው::

## አልኮል

ኖርዌይ ውስጥ በማንኛውም ቦታ ማለት ይቻላል አልኮል መጠጣት ህጋዊ ነው:: በአልኮል ተጽእኖ ስር ሆኖ መኪና ማሽከርከር ግን ህገወጥ ድርጊት ነው::

## አደንዛዥ መድሃኒቶች

በኖርዌይ የግዛት ክልል ውስጥ ማናቸውንም ዓይነት አደንዛዥ መድሃኒቶች መሸጥ ፣ ይዞ መገኘትና መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ድርጊት ነው:: እንደ ጫት ፣ ሃሺሽና ካናቢስ/ማሪዋና ያሉት አደንዛዥ ነገሮች በሌሎች አገሮች ህጋዊ ተቀባይነት ሊኖራቸው ቢችልም ኖርዌይ ውስጥ ግን በህግ የተከለከሉ ናቸው::







## ኮንትሮባንድ

ያለ ህጋዊ ፈቃድ ሸቀጦችን ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው:: በኮንትሮባንድ የገቡ ማናቸውንም ሸቀጦች መግዛትና መሸጥ በህግ ፊት ተጠያቂ ያደርጋል:: በግልዎ የኮንትሮባንድ እቃዎችን ላለመግዛት ጥንቃቄ የማድረግ ሃላፊነት አለብዎ::

## ስርቆትና የተሰረቁ ዕቃዎች

ኖርዌይ ውስጥ ስርቆት በህግ የተከለከለ ድርጊት ነው:: የሰረቀው ሰው ሌላ ቢሆንም እንኳን የተሰረቁ እቃዎችን መግዛትም ሆነ መሸጥ ህገወጥ ድርጊት ነው::

## ዝሙት አዳሪነት እና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር

ሰውን መግዛትም ሆነ መሸጥ በህግ የተከለከለ ድርጊት ነው:: ለዝሙት አዳሪነት አላማ ሲባል ሰዎችን መቅጠር ወይም ዝሙት አዳሪነት የሚያስፋፋ ድርጅቶችን መርዳት ህገወጥ ድርጊት ነው::

የእንደነዚህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች ሰለባ ከሆኑ ከዚያ ለመላቀቅ የሚያስችል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ:: በዝሙት አዳሪነት እንዲሰማሩ የሚያስገድድዎ ወይም ሊያስገድድዎ የሚሞክር ካለ ጉዳዩን ካረፋበት የጥገኝነት ጠያቂዎች ማዕከል ሠራተኞች ጋር ይነጋገሩበት:: በተጨማሪም ስለ ሁኔታው ለዩዲኣይ ማሳወቅ ይኖርብዎታል::

**በዝሙት አዳሪነት እንዲሰማሩ የሚያስገድድዎ ወይም ሊያስገድድዎ የሚሞክር ካለ ጉዳዩን ካረፋበት የጥገኝነት ጠያቂዎች ማዕከል ሠራተኞች ጋር ይነጋገሩበት:: በተጨማሪም ስለ ሁኔታው ለዩዲኣይ ማሳወቅ ይኖርብዎታል::**

ለተጨማሪ መረጃ፡-
www.politiet.no
www.lovdata.no





“በመጨረሻው ይግባኝ ወቅት ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ወደ አገርዎ መመለስ ይኖርብዎታል፡፡ አይኦኤም እንዲረዳዎት ይጠይቁ፡፡”



ምዕራፍ 6

# ወደ አገር መመለስ

**ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ ለመጨረሻ ጊዜ ውድቅ ከተደረገ ኖርዌይ ውስጥ የመቆየት መብት አይኖርዎትም:: ይህ ምዕራፍ እንዲህ ዓይነት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ የሚጠቁም መረጃ ይዟል::**

ለጥገኝነት ማመልከቻ የሚሰጠው መልስ ተፈቅዷል ወይም አልተፈቀደም የሚል ነው:: ብዙ ጥገኝነት ጠያቂዎች በኖርዌይ እንዲቆዩ ስለማይፈቀድላቸው ወደ አገራቸው ለመመለስ ይገደዳሉ::

ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ ውድቅ ሲደረግ ውሳኔው ፍትሃዊ እንዳልሆነ ሊሰማዎት ይችላል:: ብዙ ሰዎች ኖርዌይ ውስጥ ለመቆየት እንዲፈቀድላቸው የሚያደርግ በጣም አሳማኝ ምክንያት እንዳላቸው ይሰማቸዋል:: ወደ ኖርዌይ ሲሸሹ ቤት ንብረትዎን ትተው መጥተው ይሆናል:: ሆኖም ማመልከቻዎ ውድቅ መደረጉ የኖርዌይ ባለስልጣናት ለእርስዎ ጥገኝነት ለመስጠት የሚያበቃ አሳማኝ ምክንያት እንዳላገኙ ያረጋግጣል::

ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ በመጨረሻው ውሳኔ ውድቅ ከተደረገ ባለስልጣናቱ ወደ አገርዎ እንዲመለሱ ይጠብቁብዎታል:: በአብዛኛው ማመልከቻዎ ውድቅ እንደተደረገ የሚገልጸው የመጨረሻ ውሳኔ ከደረሰዎ በኋላ ባሉት ሁለትና ሶስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ አገሪቱን ለቅቀው የመውጣት ግዴታ አለብዎት::

የመጨረሻው ውሳኔ ማመልከቻዎን ውድቅ የሚያደርግ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ እርስዎም ሆኑ ቤተሰብዎ ሊያደርጉ የሚችሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት መዘጋጀት ይኖርባችኋል:: ጥገኝነት ሊያገኙ ስለሚችሉበት አጋጣሚ ከእውነታው ያልራቀ አመለካከት ሊኖርዎ ይገባል:: በተለይ ወደ ኖርዌይ የመጡት ከነልጆችዎ ከሆነ ማመልከቻው ተቀባይነት ሳያገኝ ቢቀር ምን ሊከሰት እንደሚችል ለልጆችዎ ማስረዳት ይኖርብዎታል::

### የማመልከቻ ውድቅ መደረግ

ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ ጠበቃ ይሰየምልዎታል:: ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገውን ውሳኔ በተመለከተ ይግባኝ የማለት መብትዎ የተጠበቀ ነው:: ጠበቃዎ ይግባኙን በማዘጋጀት ይረዳዎታል:: ይህንን በተመለከተ በምዕራፍ 1 ላይ ተጨማሪ ሃሳብ ያገኛሉ::

### ወደ አገር መመለስ

የመጨረሻው ውሳኔ ለጥገኝነት ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ ኖርዌይን ለቅቀው መውጣት ይኖርብዎታል:: ባረፉበት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ከሚገኙ ሠራተኞች ጋር ተገናኝተው እንዲነጋገሩ ጥሪ ይቀርብልዎታል:: ሠራተኞቹም ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ በኋላ የሚኖርዎትን አማራጮች ይነግሩዎታል::

ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ ጠበቃ ይሰየምልዎታል:: ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገውን ውሳኔ በተመለከተ ይግባኝ የማለት መብትዎ የተጠበቀ ነው:: ጠበቃዎ ይግባኙን በማዘጋጀት ይረዳዎታል::

  

**በአይኦኤም እገዛ የሚጓዙ ከሆነ የሚያወጡት ወጪ አይኖርም:: የጉዞ ሰነዶችንና የአውሮፕላን ትኬት ለማግኘት የሚያስችል እገዛም ይደረግልዎታል::**

ለመልስ ጉዞ የሚያስፈልግዎትን እርዳታና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግልዎ ለአለም አቀፉ የማይግሬሽን ድርጅት (አይኦኤም) ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ:: በፈቃደኝነት ወደ ትውልድ አገርዎ የሚመለሱ ከሆነ እርዳታ ይደረግልዎታል::

ኣይኦኤም የጉዞ ሰነዶችን እንዲያገኙ ይረዳዎታል:: በአይኦኤም አማካኝነት ሲጓዙ የሚከፍሉት ክፍያ አይኖርም::

ወጪዎችዎ በሙሉ ስለሚሸፈኑልዎትና የጉዞ ሰነድ እንዲሁም የአውሮፕላን ትኬት ለማግኘት ስለሚያስችልዎ ለአይኦኤም ጥያቄዎን ማቅረብዎ ጥቅም አለው::

ለአይኦኤም ጥያቄዎን የሚያቀርቡት ወደ አገርዎ የሚመለሱበት የጊዜ ገደብ ሳያልቅ መሆን ይኖርበታል:: ባረፉበት የመቀበያ ማዕከል ካሉት ሠራተኞች ጋር ይነጋገሩ::

## በግድ ወደ አገር ቤት መመለስ

ወደ አገርዎ የሚመለሱበት የጊዜ ገደብ ካለፈም በኋላ ከኖርዌይ ካልወጡ ጉዳይዎ ለፖሊስ ይተላለፋል:: በፈቃደኝነት ከአገር ካልወጡ በግድ ተሳፍረው እንዲወጡ ይደረጋል:: በግድ ከአገር እንዲወጡ የሚደረግ ከሆነ እርስዎን ለማስወጣት የወጣውን ወጪ ለኖርዌይ መንግስት መክፈል ይኖርብዎታል:: እነዚህን ወጪዎች ካልከፈሉ ዳግመኛ ወደ አገሪቱ እንዲገቡ አይፈቀድልዎትም::

## ወደ አገርዎ ሲመለሱ የሚደረግ የገንዘብ እርዳታ

ኖርዌይ እንዲቆዩ ፈቃድ ተሰጥቶዎት እያለም ወደ አገርዎ መመለስ የሚፈልጉ ከሆነ የገንዘብ ድጋፍ (የመመለሻ እገዛ) ሊደረግልዎ ይችላል:: ከዚህ ድጋፍ በተጨማሪ የኖርዌይ ባለስልጣናት የጉዞ ወጪዎን ይሸፍኑልዎታል::







ማመልከቻዎ ገና በሂደት ላይ ከሆነ ወይም ውድቅ ከተደረገ ይህንን እገዛ ለማግኘት ብቁ አይሆኑም፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡-
www.iom.no
www.udi.no





“የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጥዎ ስለ ኖርዌይ ብዙ ማወቅ ይጠበቅብዎታል“



ምዕራፍ 7

# በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ሲሰጥዎ



**በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ የሚሰጥዎ ከሆነ የሚኖሩበትን ቦታ ማግኘት የሚችሉበትን አጋጣሚና ሊከታተሉት የሚችሉትን የትምህርት ዓይነት ጨምሮ ምን ሁኔታ ሊያጋጥምዎ እንደሚችል ዝርዝር ማብራሪያ ያገኛሉ: :**

በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ውስጥ የተዘጋጀልዎ ማረፊያ ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ መልስ እስኪያገኝ ድረስ የተደረገ ጊዜያዊ ዝግጅት ነው: : ኖርዌይ ውስጥ ለመኖር የሚያስችል ፈቃድ ከተሰጥዎ በኋላ ግን ከጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ መውጣትዎ አይቀርም: :

## ሁለት አማራጮች ይኖሩዎታል: -

1) ከባለስልጣናቱ ምንም እገዛ ሳይደረግልዎት ራስዎ የመኖሪያ ቦታ ሊያገኙ ይችላሉ: : እንደዚያ ከሆነ በገንዘብ ራስዎን ችለው መኖር ይኖርብዎታል ማለት ነው: :

2) የመኖሪያ ቦታ ለማግኘት ከጥገኝነት መቀበያ ማዕከሉና ከኢንቴግሬሽን ኤንድ ዳይቨርሲቲ ዳይሬክቶሬት ጋር ተባብረው ሊሰሩ ይችላሉ: :

ራስዎ የመኖሪያ ቦታ ፈልገው ማግኘት ይችላሉ: : እንደዚያ ከሆነ የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ከአዲሱ ማዘጋጃ ቤት የሚደረግልዎ ድጋፍ ስለማይኖር ራስዎንም ሆነ ቤተሰብዎን ለመርዳት የሚያስችል በቂ ገንዘብ ሊኖርዎት ይገባል: :

ከሕዝብ ባለስልጣናት በሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ የሚተዳደሩ ከሆነ የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማእከሉና አይኤምዲአይ በአካባቢው ባለስልጣናት ዘንድ ማረፊያ እንዲያገኙ ይረዱዎታል: : ከአይኤምዲአይ የሚቀርብልዎ የማረፊያ አማራጭ አንድ ብቻ ነው: : ይህንን ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ከቀሩ በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ የመቆየት መብትዎን ያጣሉ: : ከዚህም በተጨማሪ የሚደረግልዎ የገንዘብ ድጋፍ ይቋረጣል: :

## የመልሶ መቋቋም ቃለ መጠይቅ

በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ እንደተሰጥዎ የሚገልጽ ማስታወቂያ ለእርስዎና ለጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ እንደደረሰ መልሶ መቋቋምን በተመለከተ ከእርስዎ ጋር ለመወያየት የሚያስችል ስብሰባ ይዘጋጃል: : የዚህ ስብሰባ ዓላማ ወደፊት ምን ለማድረግ እንደሚፈልጉ ማወቅ ነው: : ከእርስዎ ፍላጎት ጋር የሚስማማ የመኖሪያ አካባቢ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ይሆናል: : የመልሶ መቋቋሙ ቃለ መጠይቅ የመኖሪያ ፈቃዱ በተሰጥዎ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል: :

የጥገኛ መቀበያ ማዕከሉና አይኤምዲአይ የሚኖሩበትን አካባቢ ፍለጋ የሚያካሂዱት በመልሶ መቋቋም ቃለ ምልልሱ ወቅት የሰጡትን መረጃ መሰረት በማድረግ ነው: : በመሆኑም ምን ዓይነት ስራ፣ ስልጠና ወይም ተጨማሪ ትምህርት ማግኘት እንደሚፈልጉ መጥቀስዎ በጣም አስፈላጊ ይሆናል: : ከዚህም በተጨማሪ ኖርዌይ ውስጥ የሚኖር

**የባለሥልጣናቱ ድጋፍ ሳያስፈልግ የራስዎን መኖሪያ ማግኘት ይችላሉ፤ አለዚያም ከጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ እና ከአይኤምአይዲ ጋር በመተባበር ይህንኑ ማድረግ ይችላሉ::**






*የአይኤምዲአይ የአካባቢ ቢሮ በየትኛው አካባቢ እንደሚቋቋሙ ይወስናል:: አይኤምዲአይ በመልሶ መቋቋም ቃለ መጠይቁ ወቅት የሰጧቸውን ሐሳቦች ከግምት ውስጥ ለማስገባት ይጥራል::*

ቤተሰብ ወይም ዘመድ ካለዎት እንዲሁም መኖር የሚፈልጉበትን ቦታ ለመምረጥ የሚረዳ ሌላ ማንኛውም ጠቃሚ መረጃ ካለ ሊነግሩዋቸው ይገባል::

በመልሶ መቋቋም ቃለ መጠይቁ ወቅት የሚኖሩበትን አካባቢ ለማግኘት የሚሰራውን ስራ ሂደት በተመለከተ ጠቃሚ መረጃዎች እንዲያገኙ ይደረጋል::

## መልሶ መቋቋም

የአይኤምዲአይ ክልላዊ ቢሮ መልሰው የሚቋቋሙበትን መኖሪያ አካባቢ ይወስናል:: አይኤምዲአይ በመልሶ መቋቋም ቃለ መጠይቁ ወቅት የሰጧቸውን ሃሳቦች ከግምት ውስጥ ለማስገባት ይሞክራል:: ሆኖም መቶ በመቶ የእርስዎን ፍላጎት የሚያሟላ የመኖሪያ አካባቢ ማግኘት ሁልጊዜ ቀላል አይሆንም:: አይኤምዲአይ በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ላይ በመገኘት ለስራ ወይም ለተጨማሪ ትምህርት ብቁ መሆን የሚችሉበትን የመኖሪያ አካባቢ ይፈልግልዎታል:: ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ስለ መተዋወቂያ ፕሮግራሙ የሚናገረውን ክፍል ይመልከቱ::

እርስዎ የሚፈልጉትን ነገር የሚያሟላው አካባቢ የትኛው እንደሆነ ይለዩ:: ባረፉበት የጥገኝነት ጠያቀዎች መቀበያ ማዕከል ያሉት ሠራተኞች በኖርዌይ ውስጥ ስለሚገኙት የተለያዩ የመኖሪያ አካባቢዎች እንዴት መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ ሊያሳዩዎት ይችላሉ:: በሂደቱ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ከሆኑ ተስማሚ የመኖሪያ ቦታ ማግኘት ቀላል ይሆንልዎታል::

ብዙዎች ሌላ ቦታ መስፈር አይፈልጉ ይሆናል:: ወይም ደግሞ ከመጀመሪያ ምርጫቸው ያልራቀ ቦታ ለማግኘት ይፈልጉ ይሆናል::

ብዙዎች በዚያው ከተማ ውስጥ መቋቋም ይፈልጋሉ:: እያንዳንዱ የመኖሪያ አካባቢ ያለው የመልሶ መቋቋሚያ ቦታ ውስን ስለሚሆን ሁሉም ሰው መጀመሪያ በመረጠው ቦታ መስፈር አይችልም::

በአንድ የመኖሪያ አካባቢ እንዲቋቋሙ የቀረበልዎትን ምርጫ ከተቀበሉ አዲሱ የመኖሪያ ከተማዎ እርስዎን ለመቀበል ዝግጁ እስኪሆን ድረስ በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ መቆየት ይችላሉ:: በማዕከሉ የሚቆዩበት የጊዜ ርዝማኔ እንደ ሁኔታው ይለያያል::

መልሰው የሚቋቋሙበት ቦታ ሲወሰን ጉዳዩ የሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት እርስዎንና የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉን ያነጋግራል:: እንዴት መኖሪያ ቤት እንደሚዘጋጅልዎና መቼ ወደዚያ እንደሚዛወሩ እንዲያውቁ ይደረጋል:: ከዚህም በተጨማሪ ጉዞዎን በተመለከተ ሌሎች ተግባራዊ መረጃዎችን ያገኛሉ::

አይኤምዲአይ የሚያቀርብልዎ የመልሶ መቋቋም አማራጭ አንድ ብቻ እንደሚሆን ያስታውሱ:: ይህንን አማራጭ ሳይቀበሉ ከቀሩ ይደረግልዎት የነበረው የገንዘብ ድጋፍ የሚቋረጥ ከመሆኑም ሌላ ከጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ መልቀቅ ይኖርብዎታል::







## የኖርዌይን ቋንቋ መማር

በኖርዌይ የነዋሪነት ፈቃድ ለተሰጣቸው ለአብዛኞቹ ሰዎች የኖርዌይን ቋንቋ መማር መብትም ግዴታም ነው፡፡  ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ ወይም የኖርዌይ ዜግነት ለማግኘት ይህንን የቋንቋ ትምህርት ማጠናቀቅ ይጠበቅብዎታል፡፡

በኖርዌይ የመጀመሪያ ሶስት ዓመት ቆይታዎ ወቅት ይህንን የቋንቋ ትምህርት ማጠናቀቅ ይኖርብዎታል፡፡  ይህ ፕሮግራም የሚያገለግለው ከመስከረም 1 ቀን 2005 ወዲህ በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ላገኙ ሰዎች ነው፡፡

የኖርዌይን ቋንቋ መናገር መቻል ሌሎች ሰዎች የሚሉትን ለመረዳትና ሌሎች ሰዎች እርስዎ የሚናገሩትን እንዲረዱ ከማስቻሉም ሌላ ስራ ወይም ትምህርት ለማግኘት እንዲሁም በኖርዌይ ማህበረሰብ ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡  የኖርዌይን ወይም የሳሚን ቋንቋ የሚችሉ ከሆነ እንደ ግዴታ ከተቀመጠው ከዚህ የቋንቋ ትምህርት ነጻ ይሆናሉ፡፡

የኖርዌይን ቋንቋ የትምህርት ፕሮግራም በተመለከተ ሃላፊነቱን የሚወስደው የአዲሱ መኖሪያ አካባቢዎ ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ የኖርዌይን ቋንቋ ኮርስ መውሰድ ይኖርብዎ እንደሆነና እንዳልሆነ ይወስናሉ፡፡  ሊያገኙት የሚገባዎን ትምህርት ሳያገኙ ከቀሩ ቅሬታዎን የማቅረብ መብትዎ የተጠበቀ ነው፡፡

## የመተዋወቂያ ፕሮግራም

የመኖሪያ ፈቃድ ያገኙ አብዛኞቹ ሰዎች በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡  ወደ መኖሪያ ከተማዎ ከተዛወሩ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በዚህ ፕሮግራም ላይ እንዲካፈሉ ይደረጋል፡፡ ይህ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 55 የሆኑና የስደተኛነት ተሞክሮ ያላቸው አዋቂዎች እንደ መብትም እንደ ግዴታም የሚካፈሉበት የትምህርት ፕሮግራም ነው፡፡

የዚህ ፕሮግራም ዓላማ ራስዎንም ሆነ ቤተሰብዎን ለመደገፍ የሚያስችል ስራ በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ መርዳት ነው፡፡ የመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን በጋራ የሚያሳትፍ ይሆናል፡፡ የኖርዌይን ቋንቋ እንዲሁም ስለ ኖርዌይ ህብረተሰብና ስለ ስራ ልማዱ ይማራሉ፡፡

በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ላይ የሚሰጠው ትምህርት የኋላ ታሪክዎንና የወደፊቱን እቅድዎን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

የመተዋወቂያ ፕሮግራሙ በሳምንት አምስት ቀን የሚካሄድና ለሁለት ዓመት የሚዘልቅ የሙሉ ጊዜ ፕሮግራም ነው፡፡

በደሞዝ ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነና በገንዘብ ጉዳይ ራስዎን ከቻሉ ሁለት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ፕሮግራሙን አቋርጠው መውጣት ይችላሉ፡፡  ፕሮግራሙን ማቋረጥ የሚፈልጉ

**የመኖሪያ ፈቃድ ሲሰጥዎ የኖርዌይን ቋንቋ የመማር መብት ያገኛሉ፡፡ ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ ወይም ዜግነት ለማግኘት ይህንን ትምህርት ማጠናቀቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡**







**በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ላይ የሚሰጠው ትምህርት የኋላ ታሪክዎንና የወደፊት ዕቅድዎን ያገናዘበ ይሆናል።**

ከሆነ የመኖሪያ አካባቢዎ ማዘጋጃ ቤት መፍቀድ ይኖርበታል።

በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ሲሳተፉ የሚሰጥዎ ክፍያ ይኖራል። ይህ ገንዘብ በፕሮግራሙ በመካፈልዎ የሚያገኙት ደሞወዝ ነው። የመተዋወቂያ ፕሮግራሙ እንደ መደበኛ ስራ የራሱ የሆኑ ብዙ ደንቦች አሉት። ከሚያገኙት የመተዋወቂያ ክፍያ ላይ ቀረጥ መክፈል ይኖርብዎታል። በተጨማሪም ያለ በቂ ምክንያት ከቀሩ ከሚያገኙት ገንዘብ ላይ ይቆረጥብዎታል። ከመተዋወቂያው ፕሮግራም ሌላ ተጨማሪ ስራ እንዲሰሩ ይፈቀድልዎታል።

የመተዋወቂያ ፕሮግራሙን የመቆጣጠር ሃላፊነት የሚወስደው የሚኖሩበት አካባቢ ማዘጋጃ ቤት ነው። በመተዋወቂያው ፕሮግራም ላይ መገኘት እንዳለብዎትና እንደሌለብዎ የሚወስነውም ማዘጋጃ ቤቱ ነው።

በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ላይ እንዳይሳተፉ ከተከለከሉ ቅሬታዎን የማሰማት መብትዎ የተጠበቀ ነው። በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ ያሉት ሠራተኞች የመተዋወቂያ ፕሮግራሙን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ።

## ትምህርት

በኖርዌይ የነዋሪነት ፈቃድ ሲሰጥዎ በዩኒቨርሲቲ ወይም በከፍተኛ ትምህርት ኮሌጅ ገብተው እንዲማሩ ይፈቀድልዎታል። ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ከፈለጉ የተወሰኑ የመግቢያ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅብዎታል። እነዚህን መስፈርቶች በትውልድ አገርዎ አሟልተው ከነበረ በኖርዌይ ባለስልጣናት ዘንድ እውቅና እንዲሰጣቸው መረጃዎቹን ማቅረብ ይኖርብዎታል። ተጨማሪ ዝርዝር ለማግኘት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉን ሠራተኞች ወይም የጎልማሶች ትምህርት ማዕከልን ይጠይቁ።

## የግል መለያ ቁጥርና ዜግነት

የነዋሪነት ፈቃድ ሲያገኙ የኖርዌይ የግል መለያ ቁጥር ይሰጥዎታል። ይህ ቁጥር በኖርዌይ የማህበራዊ ደህንነት ክፍያ ለመፈጸም ፣ ህክምና ለማግኘት ፣ ትምህርት ወይም የስራ ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊ ነው። የግል መለያ ቁጥሩን የሚሰጥዎት ብሄራዊ የህዝብ ምዝገባ ክፍል ነው።

## የቤተሰብ ውህደት

የመኖሪያ ፈቃድ ሲሰጥዎ የቅርብ የቤተሰብ አባላት ወደ ኖርዌይ እርስዎ ዘንድ ለመምጣት ሊጠይቁ ይችላሉ። ጥያቄያቸውን ማቅረብ የሚኖርባቸው በአቅራቢያቸው ለሚገኘው የኖርዌይ ኤምባሲ ፣ ቆንስላ ወይም ለጋሲዮን ነው። በአንድ ጊዜ የሚሰጠው ፈቃድ ለአንድ ዓመት ነው።







የቅርብ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት ከሁለት ዓመት በላይ አብሮ የቆየ የትዳር ጓደኛ እና የተመዘገበ የኑሮ አጋር ፣ አብሮ የሚኖር የኑሮ ተጓዳኝ እንዲሁም ከአስራ ስምንት ዓመት በታች እድሜ ያላቸው ልጆች ናቸው:: አንዳንድ የቤተሰብ አባላትም በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል::

አብዛኛውን ጊዜ የቤተሰብ አባላትዎ ወደ ኖርዌይ እንዲመጡ ከመፈቀዱ በፊት የተወሰነ መጠን ያለው ገቢ እንዲኖርዎት ያስፈልጋል::

በቤተሰብ ውህደት ስም ወደ ኖርዌይ ለሚገቡ ሰዎችም ቢሆን የኖርዌይን የቋንቋ ትምህርት መከታተል መብትና ግዴታ ነው:: በተጨማሪም ብዙዎች በመተዋወቂያ ፕሮግራሙ ለመካፈል ብቁ ሆነው ይገኛሉ:: ይህንን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከላይ ያለውን ሃሳብ ይመልከቱ::

የቤተሰብ ውህደት ማመልከቻ ሲያስገቡ ሊከተሏቸው የሚገቡ ብዙ ጠቃሚ ደንቦች አሉ:: የሚያስፈልግዎትን መረጃ ከዩአይዲ ድህረ ገጽ (www.udi.no) ያገኛሉ:: መረጃው ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል:: ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት እርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ያረፉበትን የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ሠራተኞች ያነጋግሩ::

## አዲሱ ቤትዎ

ወደ ቤትዎ ወይም ወደ አፓርታማ ውስጥ ሲገቡ ትኩረት ሊሰጧቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች ይኖራሉ:: ቤትዎን እንዴት መያዝ እንደሚቻሉ ግራ ከተጋቡ ችግር እስኪፈጠር ድረስ ከመጠበቅ ይልቅ መጠየቅ የተሻለ ይሆናል:: በአካባቢዎ የሚገኘው አስተዳደር ሠራተኞች ለጥያቄዎ መልስ ሊሰጡዎት ይችላሉ::

## ኃላፊነት

የሚኖሩት በኪራይ መኖሪያ ከሆነ የውስጥ እድሳት ማድረግ የእርስዎ ኃላፊነት ይሆናል:: ይህ ወለሉን ፣ ግድግዳውን ፣ ኮርኒሱን ፣ የቤቱን የተገጠሙ ዕቃዎች እና ሌሌች ዕቃዎች ይጨምራል:: ቤትዎን በጥሩ ሁኔታ የማይዙ ከሆነ ለሚሰበረው ለማንኛውም ነገር መክፈል ይኖርብዎት ይሆናል::

## የአገልግሎት ክፍያ

ራስዎን ችለው ሲኖሩ በቋሚነት የሚከፍሏቸው የአገልግሎት ሒሳቦች ይኖራሉ:: እነዚህም ኪራይን ፣ ኤሌክትሪክን የቴሌቪዥን ግብር እና ስልክን ይጨምራሉ:: የሒሳብ መጠየቂያው የሚላክልዎት በየወሩ በፖስታ ይሆናል:: የኪራይ ሒሳብዎን በየወሩ መክፈል ይኖርብዎታል:: ማዘጋጃ ቤቱ ለአዲሱ ቤትዎ መብራት መስመር እንዲዘረጋ አላደረገ እንደሆነ ይህንን እርስዎ ራስዎ ተከታትለው ማስፈጸም ይኖርብዎታል::

የመኖሪያ ፈቃድ ሲሰጥዎ የቅርብ የቤተሰብ አባላት ወደ ኖርዌይ እርስዎ ዘንድ ለመምጣት ሊያመለክቱ ይችላሉ::










**ብሔራዊ የመድን ዋስትና ፕሮግራም መሥራትና የራሳቸውን ገቢ ማግኘት ለማይችሉ ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል:: የማኅበራዊ ደህንነት ጥቅሞችን ለማግኘት በርካታ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅብዎታል::**

መክፈል ያለብዎትን ሒሳብ በወቅቱ ሳይከፍሉ ከቀሩ ማሳሰቢያ ይላክልዎታል:: በዚህ ጊዜ የማሳሳቢያውን ዋጋ ጨምረው እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ:: ያም ሆኖ ያለብዎትን ሒሳብ የማይከፍሉ ከሆነ ጉዳዩ ወደ ዕዳ አሰባሳቢ ኤጀንሲ ይላካል:: ይህም ማለት ካለብዎት ዕዳ ጋር የሚመጣጠን ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ይወረሳሉ ወይም ተጨማሪ ቅጣት መክፈል ይኖርብዎታል:: በተጨማሪም በዱቤ ጥቁር መዝገብ ላይ እንዲሰፍሩ ሊደረግ ስለሚችል ወደፊት ብድር መውሰድ እንኳ ቢፈልጉ ሊከለከሉ ይችላሉ::

## የመድን ዋስትና

ቤቱንም ሆነ ያሉዎትን ንብረቶች ከእሳት አደጋ ፣ ከጎርፍ እንዲሁም ከስርቆት ለመከላከል የሚያስችል የመድን ዋስትና መግባት ይኖርብዎታል:: የመድን ዋስትና ሽፋን ካለዎት እንደተጠቀሱት ያሉ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የደረሰብዎትን አብዛኛውን ኪሳራ የሚያካክስ የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ:: የመድን ዋስትና መግባት ክፍያ ይጠይቃል::

## የእሳት አደጋ

እያንዳንዱ ቤት ውስጥ ቢያንስ አንድ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ደወልና አንድ የእሳት ማጥፊያ ሊኖር ይገባል:: የእሳት ማጥፊያው የሚያገለግለው በኤሌክትሪክ ነክ መሳሪያዎች ላይ የሚነሳውን እሳት ለማጥፋት ነው:: ከኤሌክትሪክ ጋር ዝምድና የሌላቸው የእሳት አደጋዎችን በአንድ ነገር ማፈን ወይም በውሃ ማጥፋት ይቻላል:: የእሳት አደጋ ከተነሳ 110 ደውለው የእሳት አደጋ ተከላካይ ሠራተኞችን መጥራት ይኖርብዎታል::

## ብሔራዊ የመድን ሽፋን

የኖርዌይ ብሔራዊ የመድን ዋስትና ፕሮግራም ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ብዙ የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅሞችን ያስገኛል:: አንድ ሰው ሳይገባው የማህበራዊ ደህንነት ጥቅሞችን ለማግኘት መጣሩ ወንጀል እንደሆነ ያስታውሱ::

ብሔራዊ የመድን ዋስትና ፕሮግራሙ ሠርተው የራሳቸውን ገቢ ማግኘት ለማይችሉ ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል:: የማኅበራዊ ደህንነት ጥቅሞች ተቋዳሽ ለመሆን በርካታ መስፈርቶችን ማሟላት ያስፈልጋል:: ሁሉንም እዚህ ቡክሌት ውስጥ ለመዘርዘር ቦታ አይበቃንም:: የሚያስፈልግዎትን መረጃ በአቅራቢያዎ ከሚገኘው የማኅበራዊ ደህንነት ቢሮ ማግኘት ይችላሉ:: በጣም የተለመዱት የማኅበራዊ ደህንነት ጥቅሞች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

## ከሕመም ጋር የተያያዙ ጥቅሞች

ከታመሙና ሥራ መሄድ የማይችሉ ከሆነ በዚህ ምክንያት የሚያጡትን ደሞዝ ለማካካስ የዚህ ዝግጅት ተጠቃሚ ይሆናሉ:: ከዚህ ዝግጅት ለመጠቀም እንዲችሉ ቢያንስ ለአራት ሳምንታት በቦታው ላይ የሠሩ መሆን የሚኖርብዎ ሲሆን ከሥራ ከቀሩበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ የዚህ ዝግጅት ተጠቃሚ ይሆናሉ:: ገንዘቡ የሚሰጥዎት በወሩ መጨረሻ ላይ ነው::







### ከታመመ ልጅ እንክብካቤ ጋር የተያያዙ ጥቅሞች

በእርስዎ ኃላፊነት ሥር ያለን ከ12 ዓመት በታች የሆነ የታመመ ልጅ ለመንከባከብ ብለው ከሥራ በሚቀሩበት ጊዜ ከታመመ ልጅ እንክብካቤ ጋር የተያያዙ ጥቅሞን የማግኘት መብት ይኖርዎታል:: ከዚህ ዝግጅት የሚገኘው ጥቅም የሚሰጠው በዓመት ውስጥ በአንድ ልጅ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ይሆናል::

### ከአቅም ማጣት ጋር የተያያዙ ጥቅሞች

በከባድ ሕመም ወይም በአደጋ ምክንያት መሥራት የማይችሉ ከሆነ ከጊዜያዊ የአቅም ማጣት ወይም የጉዳት ጡረታ ጥቅሞች ተካፋይ ሊሆኑ ይችላሉ:: ለተወሰነ ጊዜ መሥራት የማይችሉ ከሆነ ከጊዜያዊ የአቅም ማጣት ችግር ጋር የተያያዙ ጥቅሞች ተካፋይ ሊሆኑ ይችላሉ:: የጉዳት ጡረታ የሚከፈለው ተመልሰው ወደ ሥራ መመለስ እንደማይችሉ ከተረጋገጠ ይሆናል::

### የዕድሜ ጡረታ

ወደ ጡረታ ዕድሜ ሲደርሱ (በአብዛኛው 67 ዓመት ነው) ከመንግሥት የእድሜ ጡረታ ይታሰብልዎታል:: በጡረታ የሚያገኙት መጠን የሚመካው በሥራ ዘመንዎ ያገኙት በነበረው ገቢ ላይ ነው:: ዕድሜያቸው ከ67 ዓመት በላይ የሆኑ ማናቸውም ሰዎች መነሻውን የመንግሥት ጡረታ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው::

የዕድሜ ጡረታ እንዴት እንደሚሰላ ወይም እርስዎ ከጡረታ ምን ያህል መጠበቅ እንደሚችሉ ለማወቅ የሚፈልጉ ከሆነ በአካባቢዎ የሚገኘውን የማህበራዊ ደህንነት ቢሮ ያነጋግሩ::

### የማኅበራዊ ደህንነት ጥቅሞች

የማኅበራዊ አገልግሎቶች ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ወይም ለመከላከል ይረዳሉ:: የማህበራዊ አገልግሎቶች ሰፊ አካል የመኖሪያ ቦታ ማግኘት ላልቻሉ ሰዎች ማረፊያ የማዘጋጀት ግዴታ አለበት:: ሥራ መሥራት ወይም ራሳቸውን መደገፍ የማይችሉ ሰዎች በአካባቢያቸው ከሚገኘው የማኅበራዊ ደህንነት ቢሮ የገንዘብ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ::

ይህ እርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆነ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ማነጋገር ይኖርብዎታል:: ለእርዳታ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ::

### ለተጨማሪ መረጃ፡-

www.nyinorge.no
www.imdi.no
www.udi.no
www.velkommenoslo.no
www.aetat.no
www.skatteetaten.no
www.trygdeetaten.no



“ብቻቸውን የሆኑ ልጆች በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ ተጨማሪ እንክብካቤ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው“



ምዕራፍ 8

# ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂዎች

**ዕድሜህ ከ18 ዓመት በታች ከሆነና ወደ ኖርዌይ የመጣኸው ከወላጆችህ ጋር ካልሆነ ብቻቸውን የመጡ ጥገኝነት ጠያቂ ልጆች ከሚባሉ የተለየ ቡድን ጋር ትመደባለህ::**

ኖርዌይ ስትደርስ ጥገኝነት ጠያቂ እንደመሆንህ መጠን ምን ዓይነት ሁኔታዎች ከፊትህ እንደሚጠብቁህ ተነግሮሃል:: ለአካለ መጠን ያልደረሱና (ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች) ብቻቸውን የመጡ ልጆች የተለየ እንክብካቤና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ምን አጋጣሚዎች ከፊትህ እንደሚጠብቁህ እና በኖርዌይ በምትቆየባቸው የመጀመሪያ ጊዜያት ምን መብቶች እንደሚኖሩህ እናብራራለን::

## ብቻቸውን የመጡ ልጆች መቀበያ ማዕከል

ብቻቸውን የመጡ ጥገኝነት ጠያቂ ልጆች የተለዩ መብቶች አሏቸው:: የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከላቱ ብቻቸውን ለመጡ ልጆችና በአሥራዎቹ ዕድሜ ላሉ የተዘጋጁ የተለየ መኖሪያ አላቸው:: በእነዚህ መኖሪያዎች ሁልጊዜም ሠራተኞች አይጠፉም:: በመቀበያ ማዕከሉ ከሚሠሩት ሰዎች መካከል አንዱ የአንተ ተጠሪ ይሆናል:: በመቀበያ ማዕከሉ ያሉት ሠራተኞች ስለ አንተ ኃላፊነት ስላለባቸው በየዕለቱ የሚያስፈልግህን ነገር እንድታገኝ ይረዱሃል::

## ሞግዚት

ኖርዌይ ስትደርስ አንድ ሞግዚት ይሰየምልሃል:: ሞግዚትህ ልታገኛቸው የሚገቡህን ጥቅሞች ሁሉ ማግኘትህን ይከታተላል:: ሕጋዊና ገንዘብ ነክ የሆኑ ጥቅሞችህንም ያስከብርልሃል:: ከሞግዚትህ ልትጠብቀው ስለምትችለው እገዛ እንዲያስረዱህ በመቀበያ ማዕከሉ ያሉትን ሠራተኞች ጠይቃቸው::

## ጠበቃ

ከዚህም በተጨማሪ የጠበቃ እገዛ እንድታገኝ ይደረጋል:: ጠበቃህ በኖርዌይ ጥገኝነት እንዲሰጥህ ማመልከቻ በማስገባት ይረዳሃል:: በአብዛኛው ለቃለ ምልልስ ዩዲአይ ጋር ከመቅረብህ በፊት ከጠበቃው ጋር መገናኘት የሚኖርብህ ሲሆን ለቃለ መጠይቁ ያዘጋጅሃል:: ከዚያም ጠበቃህ ከአንተ ጋር አብሮ በመሄድ በቃለ ምልልሱ ወቅት የምትሰጠው ሃሳብ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል:: ለጥገኝነት ያቀረብከው ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ ጠበቃው ይግባኝ እንድትል ይረዳሃል:: ይህንን ሂደት በተመለከተ ምዕራፍ 1 ላይ ተጨማሪ ሃሳብ ማግኘት ትችላለህ::

## ትምህርት

በኖርዌይ የሚኖር እያንዳንዱ ልጅ ትምህርት ቤት መሄድ ይኖርበታል:: ዕድሜህ ከ6 እስከ 16 ባለው መሃል ከሆነ አንደኛ ደረጃ ወይም መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትገባለህ:: ያረፍክበት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ተስማሚ በሆነው ትምህርት ቤት ያስመዘግብሃል:: ዕድሜህ ከ16 እስከ 18 ባለው መሃል ከሆነ ደግሞ የኖርዌይን ቋንቋ የመማር መብት ይኖርሃል:: ከዚህም በተጨማሪ እስከ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶችም

**ከመቀበያ ማዕከሉ ሠራተኞች መካከል አንዱ የአንተ ተጠሪ ይሆናል:: በመቀበያ ማዕከሉ ያሉት ሠራተኞች ስለ አንተ ኃላፊነት ስላለባቸው በየዕለቱ የሚያስፈልጉህን ነገሮች በማሟላት ያግዙሃል::**







የመማር መብት ሊኖርህ ይችላል:: የዚህ ዓላማ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናውን መውሰድ እንድትችል ነው:: ባረፍክበት የጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከል ያሉት ሠራተኞች ከትምህርት ቤትህ ጋር በመነጋገር በቤት ሥራህ ረገድ የሚያስፈልግህን ድጋፍ እንድታገኝ ለማድረግ ይጥራሉ::

## የመረጃ ፕሮግራም

በትምህርት ቤት የምትማራቸው ብዙ የትምህርት ዓይነቶች ይኖራሉ:: ሆኖም ትምህርት ቤቱ የማይሸፍናቸው ልታውቃቸው የሚገቡ ነገሮች ይኖራሉ:: እንደ ጥገኝነት ጠያቂነትህ ምን መብቶችና አጋጣሚዎች እንዳሉህ ማወቅ ይኖርብሃል:: በተጨማሪም በአንዳንድ ሁኔታዎች ለራስህ ምን ማድረግ እንዳለብህ ማወቅ ያስፈልግሃል:: ባረፍክበት የመቀበያ ማዕከል ያሉት ሠራተኞች ከመረጃ ፕሮግራሙ ጋር አያይዘው ስለ እነዚህና ስለ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ይነግሩሃል::

## ዕድሜህን ማረጋገጥ

አንዳንድ አዋቂዎች ጥገኝነት ለማግኘት የተሻለ ዕድል እንደሚያሰጣቸው በማሰብ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች እንደሆነ ይናገራሉ:: ዩአይዲ የአንድን ጥገኝነት ጠያቂ ዕድሜ ለማረጋገጥ የሕክምና ምርመራ የሚያደርገው ከዚህ በመነሳት ነው:: ይህንን የሕክምና ምርመራ ለማድረግ ልትስማማም ላትስማማም ትችላለህ:: ሆኖም ይህንን ምርመራ ካላደረግህ መከራከሪያህን ሊያዳክምብህ ይችላል::

## ወላጆችን ወይም ዘመዶችን መፈለግ

ኖርዌይ ስትደርስ ወላጆችህ በሕይወት ካሉ እነርሱን ለማፈላለግ እንድትችል እገዛ ይደረግልሃል:: ሌሎች ዘመዶችንም ማግኘት እንድትችል እርዳታ ይደረግልሃል:: ቤተሰቦችህን ለማግኘት የሚጠቅም መረጃ ከሰጠህ ፍለጋውን ያቀልለዋል::

ቤተሰቦችህን ለማግኘት ምን ጥረት ማድረግ እንደምትችልና እንዴት እንደምታገኛቸው ለማወቅ ያረፍክበትን የመቀበያ ማዕከል ሠራተኞች ብታነጋግራቸው ተጨማሪ መረጃ ይሰጡሃል::

## መልሶ መቋቋም

ዩዲአይ ከጥገኝነት ጠያቂ ልጆች የሚቀርቡለትን ማመልከቻዎች ከሌሎች ይልቅ ቅድሚያ ሰጥቶ ይመረምራል:: ይህንንም የሚያደርገው በመቀበያ ማዕከሉ የምትቆይበትን ጊዜ በተቻለ መጠን አጭር ለማድረግ ነው:: ዩዲኣይ የመኖሪያ ፈቃድ ከሰጠህ በኋላ ባሉት የሦስት ወር ጊዜያት ውስጥ የአካባቢው ባለ ሥልጣናት ቋሚ መኖሪያ ይሰጡሃል::

ስለ ሁኔታህ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ባረፍክበት የመቀበያ ማዕከል ያሉትን ሠራተኞች ጠይቃቸው::

## ወደ አገር መመለስ

ወደ አገርህ መመለስ የምትፈልግ ከሆነ በጉዞ ዝግጅቶችህ እንዴት እርዳታ ማግኘት እንደምትችል ለማወቅ ያረፍክበትን መቀበያ ማዕከል ሠራተኞች አነጋግራቸው:: ለተጨማሪ መረጃ ምዕራፍ 6ን አንብብ::

## ገንዘብ

በጥገኝነት ጠያቂዎች መቀበያ ማዕከሉ በምትቆይበት ጊዜ የኪስ ገንዘብ ይሰጥሃል:: የራስህን ምግብና የሚያስፈልግህን ነገር የምትገዛ ከሆነ የምታገኘው ገንዘብ ከፍ ይላል:: ገንዘቡ የልብስ ፣ የሕክምና እና የመድኃኒት ወዘተ ወጪህን እንዲሸፍን ታስቦ የሚሰጥ ነው:: ብቻህን የመጣህ ጥገኝነት ጠያቂ ልጅ ከሆንክ ገንዘብህን የሚቆጣጠርልህ ያረፍክበት መቀበያ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ይሆናል:: ገንዘቡ ምን ላይ እንደሚውል አብራችሁ ትወስናላችሁ:: ምን ያህል ገንዘብ እንደሚደርስህ ባረፍክበት መቀበያ ማዕከል ያሉትን ሠራተኞች ጠይቃቸው::

## ለተጨማሪ መረጃ፡-

www.noas.org
www.bip.no
www.udi.no



“ይህ ቡክሌት ጠቃሚ የሆነ መረጃ ይሰጥዎታል:: የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ በጥገኛ መቀበያ ማዕከሉ ያሉትን ሠራተኞች ያነጋግሩ::“



ዲዛይንና ምክር:- ጊልሙይደን ኬይሴ ፤ ፎቶግራፍ:- ሊላን ጆናሴን ፣ ትሮንድ ኢሳክሰን ፣ የዩዲአይ የምስል ቤተ መዘክር ፤ ቅንብር:- ጆኒ ፍላድቢ

Utlendingsdirektoratet

ኖርዌጅያን ኢሚግሬሽን ዳይሬክቶሬት (UDI)
ፖስታ ሳጥን ቁጥር 8108 Dep.
ቁጥር-0032 ኦስሎ ኖርዌይ
የቢሮ አድራሻ: Hausmannsgate 21

ስልክ: +47 2335 1500
ፋክስ: +47 2335 1503
www.udi.no  www.nyinorge.no
ኢሜል: udi@udi.no